# የምርጫ ፍትህን በፍርድ ቤት ክርክር እውን ከማድረግ አንፃር በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ ሥነ-ስርዓታዊ ተግዳሮቶች ምልከታ

*በአቤኔዘር ናሆም መንገሻ*

# Examining Procedural Legal Challenges of Ethiopian Electoral Law Frameworks for Realizing Electoral Justice in Court Litigation

Abenezer Nahome Mengesha[∝]

## *አጽርኦተ ይዘት*/Abstract

*የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት የማንኛውም የዴሞክራሲያዊ ሂደት ወሳኝ ገጽታ ነው። በሚገባ የተነደፈ የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት ሁሉም ብቁ መራጮች በምርጫው እንዲሳተፉ ፣ ምርጫው ፍትሃዊ እና ግልጽነት ባለው መልኩ እንዲካሄድ ፣ ውጤቱም የመራጮችን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ እንዲሆን ይረዳል። እንዲሁም ስርዓቱ ክርክሮችን ለመፍታት የሚያስችል ውጤታማ መንገድ በማመቻቸት በምርጫ ሂደትና በዴሞክራሲያዊ ስርዓት ላይ እምነትን*

*An effective electoral dispute resolution system is crucial to any democratic process. Such a system guarantees that all eligible voters can participate, that elections are conducted fairly and transparently, and that results truly reflect the voters' will.Furthermore, it fosters trust in both the electoral process and the broader democratic system*

[∝]LLB (Bahirdar University), LLM (Wollo University), MPM; Judge at Amhara National Regional State.The author extends his gratitude to Tigistu Belay (Public Prosecutor at Addis Ababa City Adminiatration) for his invaluable comments, helpful discussions and insightful suggestions on an earlier draft of this paper. The author is also grateful to the Editor-in-Chief of BDU Journal of Law and the anonymous reviewers for their contributions to the betterment of this piece. The author can be reached at: abene400@yahoo.com

*ለመፍጠር ይጠቅማል፡፡ ስለሆነም ከዚሁ ጉዳይ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ የምርጫ ሕግ ማዕቀፍ ምን ይመስላል እንዲሁም ተግባራዊ እየተደረገ ያለው የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ከዓለም አቀፍ ህግጋትና መልካም ተሞክሮዎች አንጻር በመመዘን የስርዓቱን ምንነትና አይነት እንዲሁም የምርጫ ፍትህን በፍርድ ቤት ክርክር እውን ከማድረግ አንጻር ያሉበትን ተግዳሮቶች በግልጽ ለይቶ ማስቀመጥና በሳይንሳዊ መንገድ በጥልቀት መመርመር ተገቢ ነው የሚሆነው፡፡ ይህ ጥናት በምርጫ ወቅት የሚነሱ ክርክሮችን በፍርድ ቤት በኩል እልባት ከመስጠት አኳያ በምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓቱ ላይ ያሉ ሥነ-ስርዓታዊ ተግዳሮቶችን ምንነት ለመለየት ጽንሰ ሃሳባዊ ወይም ዶክትሪናል የምርምር ዘዴን የተጠቀመ ሲሆን በተጨማሪ አይነታዊ የጥናት ዘዴን ተከትሏል፡፡ በዚህ ጥናት በኢትዮጵያ የምርጫ ፍትህን እውን ለማድረግ ተግባራዊ እየተደረጉ ባሉ የህግ ማዕቀፎች ውስጥ በምርጫ ወቅት የሚነሱ ክርክሮችን በፍርድ ቤት በኩል እልባት ከመስጠት አኳያ ቀላል የማይባል ሥነ-ስርዓታዊ ተግዳሮቶች እንዳሉ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ እነዚህም ልዩ የምርጫ ክርክር ስነ-ሥርዓት ህግ አለመኖር፣ በምርጫ አዋጁ ላይ በፍርድ ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎች*

*by providing a clear mechanism for resolving disputes.This research examines how Ethiopian electoral law and the election dispute resolution system align with international standards and best practices. The study aims to identify the nature and type of the current system and to assess the challenges associated with achieving electoral justice through court litigation. The researcher employed a doctrinal research method to explore procedural legal challenges and analyzed selected court decisions to illustrate their practical effects. The findings indicate that significant procedural legal challenges exist within the current legal framework for ensuring electoral justice through court litigation. These challenges include: the absence of a specific procedural law addressing election*

*የመጨረሻ መሆን አለመሆንን በተመለከተ የተገለፀ ነገር አለመኖር፣ የምርጫ አዋጁ ከመራጮች ምዝገባና ከድምጽ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ስልጣን ያላቸው የትኞች የክልል እና የትኞቹ የፌደራል ፍርድ ቤት እንደሆኑ የሚመለከቱት የሚገልፀው ነገር አለመኖር እንዲሁም የዕጩዎች ምዝገባን ተከትሎ በድሬዳዋና አዲስ አበባ ለሚነሱ ክርክሮች የትኛው የፍርድ ቤት በይግባኝ መመልከት እንደሚችል ግልጽ ድንጋጌ አለማስቀመጥ የሚጠቀሱት መሆናቸውን በመግለፅ እንዲሁ አነዚህ ተግዳሮቶች በተግባር ፍርድ ቤቶቻችን ላይ እየፈጠሩ ያሉትን ፈተና ለማሳየት ይረዳ ዘንድ የተመረጡ ውሳኔዎችን በመዳሰስ ለእነዚህ ተግዳሮቶች መፍቻ ይበጃል የሚለውን የመፍትሄ ሀሳቦች ያስቀምጣል።*

***ቁልፍ ቃላት፤***  *የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት፤ የምርጫ ፍትህ፣ የምርጫ ዑደት።*

*disputes, unclear provisions in the election proclamation regarding the finality of appellate court decisions, and a lack of clarity on jurisdiction for disputes, particularly those related to candidate registration, voter registration, and the voting process in specific jurisdictions such as Addis Ababa and Dire Dawa. Based on these findings, the study proposes recommendations to enhance the effectiveness of the electoral dispute resolution system in Ethiopia.*

***Keywords****; Electoral Dispute Resolution System, Electoral Justice and Electoral Cycles*

## *መግቢያ*

ኢትዮጵያ በተለያዩ ህጎች እና ተቋማት የሚመራ ውስብስብ የሆነ የምርጫ ፍትህ ስርዓት አላት፡፡[1] የምርጫ ስርዓቷም በአብላጫ ድምፅ (plurality) ላይ የተመሰረተ ነው፡፡[2] በኢትዮጵያ ያለው የምርጫ ፍትህ ሥርዓት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ፣ የፌዴራል ፍርድ ቤቶች ፣ የክልል ፍርድ ቤቶችና የተለያዩ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች እንደየ ደረጃቸው የሚሳተፉበት ነው፡፡ ምርጫ ቦርድ ምርጫን ለማከናወን የሚያስችል አካል በአገር አቀፍ ፣ በክልል እና በአከባቢ ደረጃ የማደራጀትና የማካሄድ ኃላፊነት አለበት፡፡[3] በተጨማሪምከፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባና መሰረዝ ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን እንዲሁም የሥነ-ምግባር ጥሰቶችን ተመልክቶ ውሳኔ የመስጠት ኃላፊነት ተሰጥቶታል፡፡[4] የፌደራል ፍርድ ቤቶች በበኩላቸው በየደረጃው በተቋቋሙ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ሊፈቱ ያልቻሉትን የምርጫ ክርክሮች የመዳኘት ሃላፊነት አለባቸው፡፡ እንዲሁም ከምርጫ ቦርድና ከፌደራል ፍርድ ቤቶች በተጨማሪ በክልል ደረጃ የምርጫ ክርክሮችን የሚመለከቱ የክልል ፍርድ ቤቶችም አሉ፡፡ እነዚህ ፍርድ ቤቶች ከክልላዊ እና የአካባቢ ምርጫ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን እና አለመግባባቶችን የመፍታት ሃላፊነት አለባቸው፡፡[5] በኢትዮጵያ ያለው የምርጫ ፍትህ

[1] International Republican Institute (IRI) and National Democratic Institute (NDI), Ethiopia June 21, 2021 National Elections Report, August 05/2021, pp. 8

[2] Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, 1995, Article 79(2) (3), Federal Negarit Gazeta, Year 1, number 1. (here in after calledየኢፌድሪህገመንግስት)

[3] ዝኒ ከማሁ፣በተጨማሪም የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ፣1133/2011፣የኢትዮጵያ የምርጫ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች የምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ፣1162/2011ን ይመልከቱ፡፡

[4] የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ፣1133/2011፣አንቀጽ 148፡፡

[5] ዝኒከማሁ

ስርዓት ከግልጽነት ፣ ከገለልተኝነት እና ከተቋማት ነፃነት ጋር በተገናኙ ጉዳዮች ላይ ከዚህ ቀደም የተለያዩ አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ተቋማት እንዲሁም በጸሃፍት ትችት ይሰነዘርበት ነበር።[6] ይሁን እንጂ ቅሉ ከቅርብ ዓመታት ወዲህ ስርዓቱን ለማሻሻል ጥረት ሲደረግ ቆይቷል፤ ለምሳሌ አዲስ የምርጫ ሕግ ማውጣት፣ የምርጫ ቦርድን አቅምና ነፃነት ለማጠናከር ማሻሻያዎችን ማድረግ የሚጠቀሱ ተግባራት ናቸው።[7] ሆኖም ግን የምርጫ ውዝግቦችና ግጭቶች በኢትዮጵያ የምርጫ ሥርዓት ውስጥ ያልተቋረጡ ችግሮች ሲሆኑ ፣ ይህ አይነቱ ተግባርም በርካታ አገራዊ ፈተናዎችን ሲያስከትል ይስተዋላል።

በኢትዮጵያ የምርጫ ፍትህን እውን ለማድረግ ተግባራዊ እየተደረጉ ያሉት የህግ ማዕቀፎች በምርጫ ወቅት የሚነሱ ክርክሮችን በፍርድ ቤት በኩል እልባት ከመስጠት አኳያ ብዙ ተግዳሮቶች አሉባቸው። ከእነዚህ ውስጥ በቂ እና ግልጽ ያልሆነ የህግ ማዕቀፍ መኖር አንዱ ሲሆን ይህም በምርጫ ሕጎችና ደንቦች አፈጻጸም ላይ ውዥንብር እና ወጥነት የጎደላቸው አተገባበሮችን አስከትሎ ተመልክተናል።[8] ከዚህ ጋር በተገናኘ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ ማዕቀፍ ውስጥ እንደ ተግዳሮት ከሚወሰዱት መካከል ልዩ የምርጫ ክርክር ስነ-ሥርዓት ህግ አለመኖር፣ በምርጫ አዋጁ ላይ በፍርድ ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻ መሆን አለመሆንን

[6]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 1፣ገጽ 3-4 see also Merera Gudina, Elections and democratization in Ethiopia, 1991–2010, Journal of Eastern African Studies, Vol 5, No.4, 2011, pp. 664-680.
[7]ዝኒ ከማሁ
[8] NEBE vs Hareri Region, Federal Supreme Court Cassation Division, 2013, Case No 207036see also Balderas vs NEBE, Federal Supreme Court Cassation Division, 2013, Case No 207000

በተመለከተ የተገለፀ ነገር አለመኖር እና የምርጫ አዋጁ ከመራጮች ምዝገባና ከድምጽ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ስልጣን ያላቸው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች ያስተናግዳሉ በማለት የሚያስቀምጥ ቢሆንም ፍርድ ቤቶቹ የትኞች የክልል እና የትኞቹ የፌደራል ፍርድ ቤት እንደሆኑ የሚገልፀው ነገር የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ ላይ የዕጩዎች ምዝገባን ተከትሎ በድሬዳዋና አዲስ አበባ ለሚነሱ አለመግባባቶች የትኛው ፍርድ ቤት በይግባኝ መመልከት እንደሚችል ግልጽ ድንጋጌ አያስቀምጥም፡፡

ነገር ግን ምርጫ ተአማኒ ፣ ግልጽ እና ፍትሃዊ እንዲሆን ፣ ውጤቱም የመራጮችን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ እንዲሆን ግልፅ የሆነ የምርጫ ክርክር የሚፈታበት ስርዓትና ግልፅ የሆነ የህግ ማዕቀፍ አስፈላጊ ስለመሆኑ ሳይታለም የተፈታ ጉዳይ ነው፡፡ ይህ ጽሁፍ በኢትዮጵያ ውስጥ የምርጫ ክርክርን በፍርድ ቤት ከመፍታት ጋር በተያያዘ በምርጫ ህጎች ውስጥ ያሉትን ሥነ-ስርዓታዊ ችግሮች ለመፈተሽና ለእነዚህ ተግዳሮቶች መፍትሄዎችን ለማስቀመጥ ያለመ ነው፡፡

## 1. የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ጽንሰ-ሃሳብ አጠቃላይ እይታ

### 1.1. የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ምንነት

የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ማለት በምርጫ ሂደት ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ አለመግባባቶችን ለመፍታት የተቀመጡ ስልቶችንና ሂደቶችን በመጠቀም ከምርጫ በፊት ፣ በምርጫ ወቅት እና ከምርጫ በኋላ ለሚፈጠር አግባብ ያልሆነ ድርጊት ወይም አሰራር በህጋዊ መንገድ መቃወም የሚቻልበት ስርዓት ነው፡፡[9] ምርጫ ተአማኒ ፣ ግልጽ እና ፍትሃዊ እንዲሆን ፣ ውጤቱም የመራጮችን ፍላጎት ማንጸባረቅ እንዲችል ይህ ስርዓት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡ በተጨማሪ የምርጫ ክርክሮችን በሰላማዊ መንገድ ለመፍታት የሚያስችሉ መንገዶችን በመፍጠር የምርጫውን ታአማኒነት እና ፍትሃዊነት በማረጋገጥ የዴሞክራሲያዊ አስተዳደር ወሳኝ አካል ሆኖ ያገለግላል፡፡[10]

የምርጫ ክርክሮች ከመራጮች ምዝገባ ሂደት ፣ ከእጩዎች ምዝገባ ሂደት ፣ በድምጽ አሰጣጥ ሂደት ፣ ከድምጽ ቆጠራና ውጤት ጋር በተያያዘ ሊነሱ ይችላሉ፡፡[11] እነዚህ አለመግባባቶች ግልጽና ውጤታማ በሆነ ስርዓት እልባት የማያገኙ ከሆነ ህዝቡን በምርጫ ሂደት እና በምርጫ ውጤት ህጋዊነት ላይ ያለውን እምነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡ ስለሆነም የዴሞክራሲን መርሆዎች ለማስከበር ፣ የህግ የበላይነትን ለማረጋገጥ እና

[9] Lydia Apori Nakansa, Dispute resolution and electoral justice in Africa: The way forward, January 2015, pp.6 See also ACE Electoral Knowledge Network, The ACE Encyclopedia: Legal Framework, 2012, pp.19

[10] ዝኒ ከማሁ

[11] The International Institute for Democracy and Electoral Assistance, Electoral Justice: The International Idea Handbook, 2010, pp.37 see also Electoral justice; An Overview of the International IDEA Handbook, pp. 26 Venice Commission, opinions and reports concerning election dispute resolution, 2002, pp.31see also Barry H. Weinberg, The Resolution of Election Disputes: Legal Principles that Control Election Challenges, 2nd Edition, 2005, pp.28

የፖለቲካ መረጋጋትን ለማስፈን ውጤታማ የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት ወሳኝ ሚና አለው።[12]

የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ዋና ግብ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችል ውጤታማ ዘዴ ማቅረብ ነው። ይህ ስርዓት እንዲሁ ነፃነትን ፣ ገለልተኝነትን ፣ ግልጽነትን ፣ ተደራሽነትን እና ወቅታዊነትን ጨምሮ ቁልፍ የክርክር አፈታት መርሆችን ያስጠበቀ መሆን አለበት።[13] ከዚህ በተጨማሪ በክርክሩ ውስጥ ተሳታፊ የሆኑትን ሁሉ ፍትሃዊ ፍትህ የማግኘት መብት ፣ ማስረጃ የማቅረብ መብት እና ውሳኔ ላይ ይግባኝ የማለት መብትን በተግባር ለማረጋገጥ የሚያስችል መሆን አለበት። በዋናነት ደግሞ ክርክሩን የሚመለከተው አካል በምርጫ ሂደት ውስጥ ለሚከሰቱ አለመግባባቶች ወይም ችግሮች እልባት ለመስጠት የሚያስችሉት ተገቢ የመፍትሄ አማራጮች የተደነገጉ መሆንና ይህን ተከትሎ ከክርክር በኋላ የሚሰጡ ፍርድ ፣ ውሳኔና ትዕዛዞች ተፈጻሚነት ያላቸው መሆናቸውን ማረጋገጥ መቻል አለበት።[14] በጠቅላላው የምርጫ ክርክሮችን ለመፍታት የሚያስችል አስተማማኝና ውጤታማ ስርዓት በማቅረብ በምርጫ ሂደቱ ላይ የህዝብ አመኔታን ለማጎልበት ፣ ሊከሰቱ የሚችሉ አለመግባባቶችን ለመቅረፍ ፣ የተጠያቂነት እና የግልጽነት ዲሞክራሲያዊ እሴቶችን ለማስጠበቅ ይረዳል።

[12] ዝኒ ከማሁ
[13] The Carter Center, Guide to Electoral Dispute Resolution, 2010, pp.32
[14] ዝኒ ከማሁ

### 1.2. የምርጫ ፍትህ፣ የምርጫ ዑደቶች እና በምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት መካከል ያለው ግንኙነት

የምርጫ ፍትህ በምርጫ ሂደቶች ውስጥ ፍትሃዊነትን ፣ ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ መርሆዎችን እና አሰራሮችን የሚያመለክት ጥቅል ፅንሰ-ሀሳብ ነው፡፡[15] እንዲሁም የምርጫ ፍትህ ጽንሰ-ሀሳብ ከዲሞክራሲ መርሆዎች ጋር በቅርበት የተሳሰረ ነው፡፡ እነዚህም የመምረጥ መብት ፣ በመንግስት ውስጥ የመሳተፍ መብት ፣ ነፃ እና ፍትሃዊ ምርጫ መከወንን ያካትታሉ፡፡[16] የምርጫ ፍትህ ስርዓት የምርጫ ህጎችና ደንቦችን ፣ የመራጮች ምዝገባና ትምህርትን ፣ የዘመቻ ፋይናንስንና የምርጫ አስተዳደርን ጨምሮ የተለያዩ ጉዳዮችን ያካተተ ማዕቀፍ ነው፡፡[17] ስለሆነም የምርጫ ፍትህን ለማስፈን ግልፅ ፣ ነጻ እና ገለልተኛ የሆኑ እንዲሁም አስፈላጊ ግብአቶች የተሟላላቸው የምርጫ አስተዳደር አካላትን ማቋቋም አስፈላጊ ነው፡፡

በመሠረቱ የምርጫ ፍትህ ስርዓት የምርጫው ሂደት ፍትሃዊና ግልፅ በሆነ መንገድ እንዲካሄድ እና ውጤቱም የህዝብን ፍላጎት በትክክል የሚያንፀባርቅ መሆኑን ማረጋገጥን ግብ ያደረገ ስርዓት ነው፡፡ ይህም ሁሉም ግለሰቦች ዘራቸው ፣ ጾታቸው ፣ ጎሣቸው ወይም ማህበራዊ ኢኮኖሚያዊ ደረጃቸው ምንም ይሁን ምን የምርጫውን ሂደት በእኩልነት

[15]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 9፣ገጽ 9
[16]ዝኒ ከማሁ
[17]ዝኒ ከማሁ

እንዲገለገሉ ማድረግን ያካትታል።[18] ከዚህ በተጨማሪ የምርጫ ሂደቱ የሚመራባቸው ህጎች ግልጽና ወጥነት ያለው እንዲሆን ማድረግን ይጨምራል።[19] በጠቅላላው የምርጫ ፍትህ ስርዓት የዜጎች ድምጽ እንዲሰማና እንዲከበር ስለሚያደርግ ለዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ግንባታ ወሳኝ ነው። የምርጫ ፍትህ መርሆችን በማክበር ዴሞክራሲን ማሳደግ እና ውጤቱም የህዝቡን ፍላጎት በትክክል የሚያንፀባርቅ እንዲሆን ለማድረግ ያስችላል። እንዲሁም የምርጫ ዑደቶች ደግሞ ከቅድመ-ምርጫ ጊዜ ጀምሮ እስከ ድህረ-ምርጫ ጊዜ ድረስ ያሉትን የተለያዩ የምርጫ ደረጃዎች ያመለክታሉ። እነዚህም የቅድመ ምርጫው ጊዜ እንደ የመራጮች ምዝገባ ፣ የእጩ ምዝገባ እና የዘመቻ እንቅስቃሴዎችን ያጠቃልላል። የምርጫ ጊዜ ደግሞ እንደ ድምጽ ቆጠራ እና የውጤት ገለጻ የመሳሰሉ ተግባራትን ያካትታል። የድህረ ምርጫው ጊዜ ክርክሮችን መፍታት ፣ የመጨረሻ ውጤቶችን ይፋ ማድረግ እና የስልጣን ሽግግርን ማከናወን ያጠቃልላል።[20]

የምርጫ ዑደት የምርጫ ፍትህ ስርዓት ውጤታማነትን ለመወሰን ወሳኝ ሚና አለው ተብሎ ይታሰባል።[21] በሌላ አነጋገር አስተማማኝ የሆነ የምርጫ ፍትህ ስርዓት ግንባታ ሶስቱን የምርጫ ዑደቶች ከግምት ያስገባና ትኩረት የሰጠ ሊሆን ይገባል ማለት ነው። ምክንያቱም የምርጫ ዑደት የምርጫውን ሂደት በፍትሃዊነት፣ በግልፅነት እና በታማኝነት እንዲካሄድ

[18] KATHMANDU, Report on Electoral Dispute Resolution and Electoral Justice, 2016, pp.13 see also Parliamentary Assembly of the Council of Europe, Resolving Election Disputes in the OSCE Area: Towards a Standard Election Dispute Monitoring System, 2000, pp. 28
[19] ዝኒ ከማሁ
[20] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11፣ገጽ 8
[21] ዝኒ ከማሁ

የሚያስችል ተግባራዊ ማዕቀፍ በመሆኑ እንዲሁም የምርጫ ዑደት የምርጫ ፍትህ ስርዓት አንዱ አካል በመሆኑ ነው፡፡[22] በጠቅላላው ፣ ምርጫዎች ነጻ ፣ ፍትሃዊ እና ግልጽ እንዲሆኑ የምርጫ ፍትህ ስርዓቱ ውጤታማ መሆን ወሳኝ ጉዳይ ነው፡፡ እንዲሁ የምርጫ ፍትህ ስርዓቱ ደግሞ ውጤታማ ለመሆን ሶስቱን የምርጫ ዑደቶች የምርጫው ሂደት በሂደቱ ላይ እምነት በሚያሳድር መልኩ እንዲካሄድ እና ውጤቱም የህዝቡን ፍላጎት በትክክል የሚያንፀባርቅ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚያስችል ማዕቀፍ መዘርጋት ይጠበቅበታል፡፡[23] ስለሆነም በምርጫ ዑደቱ በሙሉ የምርጫ ፍትህ መርሆችን በማክበር ዴሞክራሲን ማሳደግ እና የዜጎች ድምጽ እንዲሰማ እና እንዲከበር ማድረግ ያስችላል፡፡[24]

ከዚህ ጋር በተያያዘ በምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ፣ በምርጫ ዑደቶች እና በምርጫ ፍትህ መካከል ያለው ግንኙነት ውስብስብ እና ሰፋ ያለ ነው፡፡ ከላይ እንደተገለፀው የምርጫ ፍትህ በምርጫ ሂደቶች ውስጥ ፍትሃዊነትን ፣ ግልፅነትን እና ተጠያቂነትን የሚያረጋግጡ መርሆዎችን እና አሰራሮችን የሚያመለክት ጥቅል ፅንሰ-ሀሳብ ሲሆን የምርጫ ዑደቶች ደግሞ በምርጫ ፍትህ ስርዓት ውስጥ የታቀፉ ከቅድመ-ምርጫ ጊዜ ጀምሮ እስከ ድህረ-ምርጫ ጊዜ ድረስ ያሉትን የተለያዩ የምርጫ ሂደቶችን የሚያሳይ ነው፡፡ እንዲሁም የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ደግሞ በምርጫ ዑደት ውስጥ የሚታቀፍ ሆኖ በምርጫ ሂደት ውስጥ የሚነሱ ግጭቶችን ፣ ክርክሮችን

[22] ዝኒ ከማሁ
[23] ዝኒ ከማሁ
[24] ዝኒ ከማሁ

ወይም አለመግባባቶችን ለመፍታትና ለማስተካከል የተቀመጡ ስልቶችን እና ሂደቶችን የሚያመለክት ነው፡፡ ስለዚህም የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት በምርጫ ዑደት ውስጥ ያለ የምርጫ ፍትህን ለማስፈን የማይተካ ሚናን የሚጫወት ስርዓት ነው ለማለት ይቻላል፡፡ ምክንያቱም በምርጫ ወቅት የሚነሱ አለመግባባቶች በምርጫው ሂደት ታማኝነት እና በምርጫው ውጤት ላይ ከፍተኛ ተጽእኖ ይኖራቸዋል፡፡ ስለሆነም እነዚህን ክርክሮች በጊዜ ፣ ፍትሃዊ እና ግልጽ በሆነ መንገድ የህግ የበላይነትን በተከተለ መልኩ መፍታት አስፈላጊ ነው የሚሆነው፡፡ ይህም መደረጉ ሁሉም ግለሰቦች በምርጫው ሂደት ውስጥ የመሳተፍ እኩል እድል እንዲያገኙ እና የምርጫው ውጤት በትክክል የህዝብን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ እንዲሆን ይረዳል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ በዋናነት የምርጫ ዑደቶች የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓትን ተፈጥሮ እና ስፋት በመቅረጽ ረገድ ጉልህ ሚናን ይጫወታሉ፡፡[25] ምክንያቱም የምርጫ ዑደት አንዱ ክፍል የሆነው የቅድመ ምርጫ የዝግጅት ምዕራፍ የምርጫ ሕጎችን ፣ ደንቦችንና ሥነ-ስርዓቶችን ፣ እንዲሁም ሊከሰቱ የሚችሉ ክርክሮችን መለየትና ለመፍታት የሚያስችሉ ዘዴዎችን ማዘጋጀትን የሚጠይቅ በመሆኑ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የምርጫ ዑደት የትግበራ ምዕራፍ ደግሞ እነዚህን ሕጎች ፣ ደንቦች እና ሥነ-ስርዓቶችን መተግበር እንዲሁም በምርጫው ወቅት ለሚነሱ ክርክሮች መፍትሄ መስጠትን ያካትታል፡፡ እንዲሁ ደግሞ ከትግበራ ምዕራፍ ቀጥሎ

[25] ዝኒ ከማሁ

የሚመጣው የግምገማ ምዕራፍ የምርጫውን አጠቃላይ ሁኔታ ግምገማ ፣ ማንኛውንም ክርክሮች መፍታት እና የምርጫ ሂደቱን ለማሻሻል አስፈላጊ የሆኑ ማሻሻያዎችን ተግባራዊ ማድረግን የሚያካትት በመሆኑ ነው፡፡[26]

ከዚህ ጋር በተገናኘ በምርጫ ዑደት ውስጥ የምርጫ ፍትህን ለማስፈን ፣ ውጤታማ የሆኑ የምርጫ ክርክር አፈታት ሂደቶች በሁሉም የምርጫ ዑደት ደረጃዎች ውስጥ መካተት አለባቸው፡፡ ይህም ክርክሮችን ለመፍታት ግልጽና ፍትሃዊ አሰራርን መዘርጋት ፣ እንዲሁም የመፍትሄውን ሂደት የሚደግፉ በቂ ግብአቶችን ማዘጋጀት ይጠይቃል፡፡

በጠቅላላው ፣ በምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ፣ በምርጫ ዑደቶች እና በምርጫ ፍትህ ስርዓት መካከል ያለው ግንኙነት ዘርፈ ብዙ ነው፡፡ በሁሉም የምርጫ ዑደት ደረጃዎች ውስጥ ክርክርን ለመፍታት የሚያስችል ውጤታማ ዘዴዎችን በማቅረብ እና የህግ የበላይነትን በማስከበር የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ሂደቶች ሁሉም ግለሰቦች በምርጫ ሂደት ውስጥ የመሳተፍ እኩል እድል እንዲያገኙ እና የምርጫው ውጤት በትክክል የህዝብ ፍላጎት የሚያንፀባርቅ መሆኑን ለማረጋገጥ ያስችላል፡፡

### 1.3. የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት መርሆዎች እና ጥበቃዎች

አገራት የትኛውንም ዓይነት የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ተግባራዊ ቢያደርጉ ነፃ ፣ ፍትሃዊና እውነተኛ ምርጫ እንዲካሄድ ለማስቻል ይህ

[26]ዝኒ ከማሁ

ስርዓት የሚመራባቸውን መርሆዎችና ጥበቃዎችን በግልፅ ማስቀመጥና ተግባራዊ ማድረግ የግድ ይላቸዋል፡፡[27] እነዚህ መርሆዎች እና ጥበቃዎች የምርጫ ክርክርን ለመወሰን ስልጣን የተሰጠው የመጨረሻ አማራጭ በሆነው አካል ብቻ ሳይሆን በምርጫ ክርክር ላይ ውሳኔ የሚያሳርፉ አካላት ማለትም ከመጀመሪያው ውሳኔ ሰጪ አካል ጀምሮ በየደረጃው ባሉት ውሳኔ ሰጪ አካላት ሊተገበሩ ይገባል::[28] ከመርህ ጋር በተያያዘ የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት ምርጫ ነፃ፣ ፍትሐዊና እውነተኛ በሆነ መንገድ መከናወን አለበት የሚለውን መርህ እንዲሁም ደግሞ ጠቅላላ የሆኑ በተለያዩ የህግ ሂደቶች ላይ ተፈጻሚ የሚደረጉትን እንደ ህገ-መንግስታዊነት፣ ህጋዊነት፣ የዳኝነት ነፃነትና ፍትሃዊ ዳኝነት መርሆዎችን እውቅና የሰጠ እና የተቀበለ መሆን አለበት፡፡[29] ከዚህ በተጨማሪ ለምርጫ ክርክር ብቻ በልዩ ሁኔታ ተፈፃሚ የሚደረግ መርህ ያለ ሲሆን ይህም ፣ ያለመሻር መርህ( principle of irrevocability) በመባል ይታወቃል፡፡[30] በዚህ መርህ መሰረት የምርጫ ሂደት ተከታታይ ደረጃዎች የሚጠናቀቁበት ቁርጥ ባለ የጊዜ ገደብ ተደንግጎ መቀመጥ አለበት የሚል ሲሆን ፣ የትኛውም የተለየና የተቀመጠ ደረጃና የጊዜ ገደብ ከተጠናቀቀ በኋላ (ለምሳሌ የምርጫው የቅድመ ዝግጅት ደረጃ) ፣ ከተወሰነ የጊዜ ገደብ በኋላ ቀጥሎ በሚመጣው ወይም በኋለኛው ደረጃ (ለምሳሌ በምርጫ ቀን ወይም

---

27 Barry H. Weinberg, The Resolution of Election Disputes: Legal Principles that Control Election Challenges, 2nd Edition, 2005, pp.38 see also Electoral Dispute Resolution Discussion Paper Experts Meeting, Atlanta GA – February 2009, pp.63 see also ODIHR publication, Resolving Election Disputes in the OSCE Region 2000, pp.49

28 ዝኒ ከማሁ

29 ዝኒ ከማሁ

30 የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11

በድህረ-ምርጫ ደረጃ) ወቅት ስለ መጀመሪያው ደረጃ (የምርጫው የቅድመ ዝግጅት ደረጃ) ለተደረጉ ድርጊቶች ወይም ውሳኔዎች ምንም ተጨማሪ የመከራከር እድል ሊሰጥ አይገባም የሚል ነው፡፡[31]

ነገር ግን፣ በአንዳንድ የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓቶች ውስጥ ለእንደዚህ አይነቱ መርህ ልዩ ሁኔታዎች ተቀምጠው ሲያገለግሉ ይስተዋላል፡፡ ለምሳሌየምርጫ ሂደትን የሚቆጣጠረው አካልምንም እንኳን በምርጫው ዝግጅት ወቅት እጩ ተመራጭ ለመሆን የሚያስፈልጉትን መስፈርቶች የሚያሟሉ መሆናቸውን በማረጋገጥ የመዘገበ ወይም በእጩነት የቀረቡትን እጩዎች ያሳለፋቸው ቢሆንም፣ ይህን በተመለከተ በእጩነት የተመዘገቡት ግለሰቦች ወይም ፓርቲዎች በእጩነት ሊመዘገቡ አይገባም የሚል ቅሬታ በድጋሚ ቀርቦ የምርጫው አሸናፊ ከመታወጁ በፊት በድህረ ምርጫው እንደገና ሊታይ እንደሚችል እና የምርጫ ክርክርን በሚመለከተው አካል በድጋሚ ውሳኔ እንዲያገኙ ሊደረግእንደሚችል ሲያስቀምጡ ይስተዋላል፡፡[32]

የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ጥበቃዎች ማለት የመራጮችን መብት ለማስከበር ሲባልየምርጫ ተቋማት እሴቶችና መብቶችን፣ እንዲሁም ተቋማት ራሳቸውን የሚጠብቁበት፣ የሚደገፉበትና፣ ራሳቸውን የሚከላከሉበት ማንኛውም ህጋዊ ጥበቃ እና አሰራር ነው፡፡[33] የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት መዋቅራዊም ሆነ ስነ-ሥርዓታዊ ጥበቃዎች አላማ ምርጫዎች በህግ አግባብ እንዲካሄዱ እንዲሁም ነፃ፣ ፍትሃዊ እና

[31]ዝኒ ከማሁ
[32]ዝኒ ከማሁ
[33]ዝኒ ከማሁ

እውነተኛ እንዲሆኑ ለማስቻል ነው፡፡[34] ከዚህ በተጨማሪ የመራጮችንም ሆነ የተመራጮችን የምርጫ መብቶች የማስጠበቅ አለማ እንዳለው ለመገንዘብ ይቻላል፡፡ ስለሆነም ከዚህ አንፃር ጥሩና ውጤታማ የሆነ የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት ለዴሞክራሲ ሥርዓት መጎልበትና የሕግ የበላይነት መከበር ዋስትና ይሆናል ለማለት ያስችላል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ዜጎች፣ እጩዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች፣ ሚዲያዎች፣ ባለስልጣኖች እና በምርጫ ሂደት ውስጥ ሚና የሚጫወቱት ሁሉ በጠቅላላው የምርጫ ህግን በራሳቸው ፈቃድ ማክበር የሚጠበቅባቸው ቢሆንም ቅሉ የምርጫ ህጉ እንዲከበር እና ህጉን የሚጥሱ ተግባሮችና አሰራሮችን ለመቅረፍ የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ቁልፍና የማይተካ ሚና አለው፡፡ ከምንም በላይ ደግሞ የምርጫ ተግባራት ክንውኖች፣ ሂደቶች እና ውሳኔዎች ከምርጫ ህጉ እና ከሌሎች ህጎች ጋር የተጣጣሙ መሆናቸውን ለማረጋገጥ የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት እጅግ በጣም አስፈላጊ ነው፡፡[35]

በምርጫ ወቅት የሚነሱ ቅሬታዎችን በህጋዊ መንገድ እንዲፈቱ ከሚያስችሉት ጥበቃዎች መካከል መዋቅራዊ እና ስነ-ሥርዓታዊ ጥበቃዎች ዋነኞቹ ተደርገው ይወሰዳሉ፡፡ መዋቅራዊ ጥበቃ ማለት የምርጫ ክርክሮችን ለመመልከት ስልጣን የተሰጠው አካል በነፃነት እና በገለልተኝነት መስራቱን ለማረጋገጥ የሚያገለግል የህግ ጥበቃና ከለላ

[34] ዝኒ ከማሁ

[35] International Foundation for Electoral System, Guidelines for Understanding, Adjudicating, and Resolving Disputes in Elections, 201, pp. 50see also, Parliamentary Assembly of the Council of Europe, Handbook for the Observation of Election Dispute Resolution, 2019

ነው፡፡[36] እንዲሁም ስነ-ሥርዓታዊ ጥበቃዎች ማለት ደግሞ በምርጫ ወቅት በምርጫ ሂደቱም ሆነ ውጤቱ ላይ የሚፈጠሩ ቅሬታዎችን የምርጫ ክርክሮች ለመመልከት ስልጣን ለተሰጠው አካል ለማቅረብ እና የተፋጠነ መፍትሄ እንዲያገኙ ለማድረግ የተቀመጡ ስልቶች ሲሆኑይሕም የምርጫ ፍትህ እውን እንዲሆን መንገድ የሚጠርጉ እና የክርክር አፈታት ስርዓቱ ውጤታማ እና ቀልጣፋ መሆኑን ለማረጋገጥ የሚረዱ ህጋዊ ጥበቃዎች ናቸው፡፡[37] በጠቅላላው የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት መርሆዎች እና ጥበቃዎች የምርጫውን ሂደት ታማኝነት ፣ ፍትሃዊነት እና ትክክለኛነት ለማረጋገጥ የተነደፉ ንድፎች ናቸው ለማለት ያስችላል። በመቀጠልም ከዚህ በታች ባለው ክፍል ከጽሁፉ ጋር ጥብቅ ቁርኝት ያለውን የምርጫ ክርክርን ለመፍታት የሚያገለግሉ ቁልፍ ሥነ-ስርዓታዊ ጥበቃዎችን በዝርዝር ለማየት እንሞክራለን።

### 1.3.1. የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት ስነ-ሥርዓታዊ ጥበቃዎች

ስነ-ሥርዓታዊ ጥበቃዎች የምርጫ ፍትህን የሚያጎለብቱና የሚጠብቁ ዋስትናዎች ሲሆኑበመሰረታዊነት ደግሞ ስነ-ሥርዓታዊ ጥበቃዎች በመደበኛነት የሚቀመጡትን የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓቶች ተደራሽ ፣

[36]ዝኒ ከማሁ
[37]ዝኒ ከማሁ

ውጤታማ እና ቀልጣፋ መሆናቸውን ለማረጋገጥ ነው፡፡[38] ማንኛውም የምርጫ ክርክር አፈታት ሂደት የመራጮችንና የተመራጮችን የመምረጥ እና የመመረጥ መብታቸውን ለመጠበቅ ወይም ለመከላከል ለሚፈልጉ ሰዎች ወይም ፓርቲዎች ተደራሽ መሆን አለበት፡፡ይህ ማለትምሂደቱ ከክፍያ ነፃ ወይም በአነስተኛ ክፍያ እንዲገኝ ማስቻል እንዲሁም በሂደቱ ውስጥ ቀላል ፣ ፈጣን እና ወቅቱን የዋጀ ጥበቃን በማድረግ ለመምረጥና መመረጥ መብት ዋስትናን መስጠት ወይም በአጠቃላይ ሁኔታ የምርጫ ህግ ማዕቀፎችን በመተላለፍ የሚጣሰው መብት ወደነበረበት መመለስ ከማይችልበት ደረጃ ከመድረሱ በፊት ለመመለስ የሚያስችል ስነ-ሥርዓታዊ ጥበቃን የሚያደርግ ነው፡፡[39] ከእነዚህ ውስጥም በጥቂቱ፤

## ሀ. ግልጽ፣ የማያሻማ እና ቀላል የሆኑ ድንጋጌዎች መኖር

ጥሩ የሚባል የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ንድፍ የድንጋጌዎችን በግልጽ፣ በማያሻማ እና ቀላል በሆነ መንገድ መቀመጥን ይጠይቃል፡፡ የምርጫ ሕግ ማዕቀፎች እና የምርጫ መብቶች መከበርን የሚጠብቁ የሕገ-መንግሥት፣ የአዋጆች እና ሌሎች ህጎች ድንጋጌዎች የፍትህ ተደራሽነት እና የተገማችነት መስፈርቶችን ለማሟላት ያስችላቸው ዘንድ በቀላል እና ግልጽ በሆነ ቋንቋ መዘጋጀት መቻል አለባቸው፡፡[40] እንዲሁም

[38] ዝኒ ከማሁ

[39] ዝኒ ከማሁ

[40] Venice Commission, opinions and reports concerning election dispute resolution, 2002, pp.31see also Barry H. Weinberg, The Resolution of Election Disputes: Legal Principles that Control Election Challenges, 2nd Edition, 2005, pp.28 see also Electoral Dispute

ይዘታቸው ምርጫው በሚካሄድበት የማህበረሰብ ቋንቋ በሰፊው ተባዝቶ መሰራጨት የሚጠበቅበት ሲሆን ይህም ሁሉም ፍላጎት ያላቸው ሰዎች በግልፅ እና በቀላሉ እንዲረዱት እና ቀጣይነት ባለው መልኩ እንዲከተሉ ለማስቻል ነው፡፡[41]

አሻሚ፣ ግልጽ ያልሆኑና፣ ያልተሟሉ የሕግ ድንጋጌዎች መኖር በምርጫ ሂደት ላይ የሚነሱ ህገወጥ ተግባራትን በመቃወም በምን አግባብ እንደሚቀርቡና ለየትኛው አካል እንደሚቀርቡ ግራ መጋባትን ሊፈጥር ይችላል፡፡ እንዲህ ዓይነቱ ውዥንብር የምርጫ ፍትህ ስርዓትንይጎዳል፣ እናም በመጨረሻ ለማታለል እና ህገወጥ ለሆኑ ተግባራት በር ሊከፍት ይችላል፡፡[42] ከዚህ በተጨማሪ የምርጫውን ሂደት እና ፍትህን ከማደናቀፍ በዘለለ የተመረጡ እጩዎች ሃላፊነታቸውን ተረክበው ስራቸውን ከመጀመር እንዲዘገዩ እና በህጋዊነታቸው ላይ ጥላ እንዲያጠላያደርጋል፡፡[43]

ከላይ እንደተገለጸው የዳኝነት ስልጣኑ የማን እንደሆነ በህግ ግልጽ ካልሆነየምርጫ ክርክሮችን ለመመልከት ስልጣን የተሰጠው አካል ቅሬታ የሚያቀርበውን ወገን ለመስማት ስልጣን እንደሌለው የሚቆጥርበት ወይም ቅሬታውን ተቀባይነት እንደሌለው የሚቆጥርበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችላል፡፡

---

Resolution Discussion Paper Experts Meeting, Atlanta GAFebruary 2009፣ see also ODIHR publication, Resolving Election Disputes in the OSCE Region 2000

[41] Oliver Joseph and Frank McLoughlin the Electoral Justice System Assessment Guide, 2019, pp.50 see also Ellena, K., Elections on Trial: The Effective Management of Election Disputes and Violations (Washington, DC: International Foundation for Electoral Systems: 2018), <https://www.ifes.org/publications/elections-trial-effective-management-election-disputes-and-violations>, accessed 12 January 2024

[42]ዝኒ ከማሁ

[43]ዝኒ ከማሁ

ከዚህ ጋር በተያያዘየምርጫ ህግ የትኞቹ በምርጫ ቅሬታ ላይ የሚሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻ እንደሆኑ እና የትኞቹ ደግሞ በድጋሚ ስልጣን ለተሰጠው አካል ሊቀርቡ እንደሚችሉና የትኛው አካል ቅሬታዎችን በድጋሚ አይቶ የመጨረሻ ውሰኔ መስጠት እንደሚችል በግልፅ ማስቀመጥ ይጠበቅበታል፡፡[44] በጠቅላላው የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓትን የሚመሩ ሥነ-ስርዓታዊ ሕጎች ስብስብ ወጥነት ያለው እና የተሟላ፣ ግልጽ በሆነ ቋንቋ የተዘጋጀ፣ የዘፈቀደ ትርጓሜዎች አደጋን የሚያስወግድ እና የምርጫ ክርክርን የሚመለከተው አካል ያለማቋረጥ ተግባራዊ የሚያደርገው መሆን አለበት፡፡

## ለ. የተሟላ እና ውጤታማ የምርጫ ፍትህ ማግኘት

በምርጫ ሂደት ውስጥ ማንም ሰው በምርጫ ሕጉ ዕውቅና ያለው መብትና ጥቅሙ በባለስልጣኑ ወይም በሌላ አካል በሚወስደው እርምጃሲጎዳ እራሱንና መብቱን ለመከላከል የሚያስችለው ስርዓት ሊኖር የግድ ይላል፡፡[45] ከዚህ ጋር በተያያዘ ዜጎች፣ እጩዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች እና የፖለቲካ ቡድኖች በፆታ እና በብሔር ላይ የተመሰረተ ልዩነት ሳይደረግባቸው ቅሬታና በደሎቻቸውን ማቅረብ እንዲችሉ የምርጫ ክርክር አፈታት ሂደቶች በጊዜ፣ ርቀትና ወጪ ተደራሽ መሆን አለባቸው፡፡ እንዲሁም ዜጎች ምክንያታዊ ባልሆኑ ስነ-ሥርዓታዊ ቅድመ ሁኔታዎች፣ መስፈርቶች

[44]ዝኒ ከማሁ
[45]ዝኒ ከማሁ

ወይም መሰናክሎች ሳይገደቡ ውጤታማና እና ፈጣን ውሳኔ ማግኘት መቻል አለባቸው::[46]

ከምንም በላይ የውጤታማ የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት መገለጫ ባህሪያት ከሆኑት ውስጥ አንዱ መብቶችን በመተላለፍ ጥሰት ሲፈጸም ጥሰቱን መከላከል የሚቻልበት ቀልጣፋ ሂደት መኖሩ እና ከምርጫ ሂደት ጋር የተያያዘ እያንዳንዱ እርምጃ እና ውሳኔ በህግ ማዕቀፉ ውስጥ እንዲከናወኑ ማስቻላቸው ነው::[47]

ከዚህ ጋር በተገናኘ ገለልተኛ በሆነ ፍርድ ቤት ውጤታማ መፍትሄ የማግኘትመብት በባለ ብዙ ወገን አለማቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶች እና በአብዛኛዎቹ የዲሞክራሲያዊ ስርዓት ተከታይ ሀገራት ህገ-መንግስት ውስጥ ተደንግጎ ይገኛል::[48] በተጨማሪም የምርጫ ፍትሕመሠረታዊ የሰብዓዊ መብት በመሆኑ በአንድ አገር ባሉ ህግጋቶች ውስጥ በበቂ ሁኔታ ካልተረጋገጠ ወይም እውቅና ካልተሰጣቸው እንኳን ያቺ አገር አባል በሆነችባቸው ዓለም አቀፍ የሰብአዊ መብት ሰነዶችና ስምምነቶች የተደነገጉትን ዓለም አቀፍ ስምምነት መሰረት በማድረግ ለማረጋገጥ ይቻላል:: በጠቅላላው በምርጫ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለሚመለከተው አካል ለማቅረብ ቀላልና ቀልጣፋ አሰራር መኖር አለበት፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ቅሬታዎች ሲፈጠሩ ቅሬታ ያለው አካል አቤቱታውን

[46] Katherine Ellena, Chad Vickery and Lisa Reppell, Elections on Trial: The Effective Management of Election Disputes and Violations, 2018, pp.13 see also KATHMANDU, Report on Electoral Dispute Resolution and Electoral Justice, 2016, pp.42

[47]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 27

[48]ዝኒ ከማሁ

ለሚመለከተው ባለስልጣን ለማቅረብ እንዲችል፤ ክርክሩን የሚመለከተውን ባለስልጣን እዛው በአካባቢው ማግኘትና ቅሬታውን ማቅረብ መቻል አለበት፡፡ ይህም የምርጫ ፍትህ መብትን አካባቢያዊ በማድረግ ተደራሽነቱን ይበልጥ በማስፋት ጥበቃ እንዲሰጥ ያስችለዋል፡፡

## ሐ) የምርጫ ፍትህን በነጻ ወይም በተመጣጣኝ ዋጋ ማግኘት

የምርጫ ፍትህ የማግኘት መብት ፍትሃዊ ውሳኔ የማግኘት መሰረታዊ መብት አካል እንደመሆኑ መጠን የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ሂደት ከክፍያ ነፃ ወይም በተመጣጣኝ ዋጋ መቅረብ አለበት ተብሎ ይታሰባል፡፡[49] ከዚህ ጋር በተያያዘ የምርጫ ክርክርን ለመመልከት ስልጣን ላለው አካል ቅሬታን ለማቅረብ ምንም ዓይነት የገንዘብ ክፍያ በቅድመ ሁኔታነት የማይካተት ከሆነ የምርጫ ፍትህ በነፃ ተደራሽ ሆኗል ለማለት ያስችላል፡፡ እንዲህ አይነቱ ጥበቃ የቅሬታ አቅራቢው የገንዘብ አቅምሁኔታ ምንም ይሁን ምን ፍትህ የማግኘት መብትን ያከበረ እንዲሆን ያደርገዋል፡፡

ብዙ ሀገራት የምርጫ ፍትህ የማግኘት መብትን እንደ ሰብአዊ መብት በመመልከት በህጋቸው ማንኛውም የሚቀርብ የምርጫ ቅሬታ ያለ ምንም ክፍያ በነጻ እንዲያቀርቡየሚያደርጉ ሲሆን የዚህንም ወጪ ከመንግስት ግምጃ ቤት እንዲሸፈን በማድረገ ጭምር ስለመሆኑ ለመረዳት ይቻላል፡፡[50] አንዳንድ ጊዜ ደግሞ ክፍያን በቅድመ ሁኔታነት በሚያስቀምጡ ስርዓቶች

[49] OSCE Office for Democratic Institutions and Human Rights, Handbook for the Observation of Election Dispute Resolution,2019, pp.80
[50]ዝኒከማሁ

ውስጥ እንዲሁ የሕዝብን ጥቅም የሚመለከቱ የምርጫ ክርክሮች በሚሆኑ ጊዜ ክፍያዎች መንግሥታዊ ባልሆኑ ድርጅቶች እና የሲቪል ማህበረሰብ ድርጅቶች ሲሸፈኑ ይስተዋላል፡፡[51] ከዚህ በተጨማሪ የምርጫ ቅሬታዎችን ለማቅረብ የክፍያ ቅድመ ሁኔታ እንዲኖራቸው ሲደረግ የፍትህ ስርዓቱ ተገልጋዮች አገልግሎቱን በተመጣጣኝ ዋጋ እንዲያገኙ ወይም የሚከፈለው ክፍያ የተመጣጣኝነት መርህን ያገናዘበ ስለመሆኑ መረጋገጥ መቻል አለበት፡፡[52] ይህ ማለትም የሚጣለው ክፍያ የምርጫ ፍትህ ለማግኘት እንቅፋት በሚሆን ደረጃ መጣል የለበትም ማለት ነው፡፡

**መ) ወቅቱን የጠበቀ መሆን**

የምርጫ ክርክሮችን ለሚመለከተው አካል ቅሬታ ለማቅረብና ውሳኔ ለማግኘት በጠቅላላው ለፍርድ ቤት ሙግቶች እና ለሌሎች የአስተዳደር ነክ ክርክሮች ከሚቀመጡት ጊዜ ገደብ ያጠረ ምክንያታዊ የሆነ የጊዜ ገደብ መቀመጥ አለበት ተብሎ ይታሰባል፡፡[53] እነዚህ የሚቀመጡት ጊዜ ገደቦች በአንድ በኩል በምርጫው ላይ የተነሱ ቅሬታዎችን ይዘቱንና አግባብነቱን በጥልቀት ለመመርመር እና ማስረጃዎችን ለመስማት የሚያስችሉ እንዲሁም በሌላ በኩል ደግሞ ጉዳት የደረሰበትን አካል የተፋጠነ ፍትህ

[51]ዝኒከማሁ
[52]ዝኒ ከማሁ
[53]ዝኒ ከማሁ

የማግኘት መብትን ባከበረ መልኩ ሚዛን ጠብቆ ለማስኬድ የሚያስችሉ መሆን አለባቸው፡፡[54]

የምርጫ ክርክርአፈታት ስርዓት ሂደቶች ጊዜ ገደብ ያስቀመጡ መሆን አለባቸው ፡፡ያም ማለት በህጋዊ መንገድ በተቀመጡት የምርጫ ሂደቶች ወይም ደረጃዎች ውስጥ በተቀመጠው ጊዜ ገደብ ውስጥ ውሳኔ መሰጠት አለበት ማለት ነው፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ እንዲሁ በህግ ከተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውጭ የሚሰጠው ውሳኔ ፍትሃዊ ላይሆን ይችላል፡፡ ምክንያቱም የሚሰጠው ውሳኔ ከዘገየ በእያንዳንዱ የምርጫ መብቶች ላይ የሚደርሰውን ጉዳት ለማስተካከል የማይቻል እንዲሆን ሊያደርገው ይችላል፡፡[55]

የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት የተለያዩ የምርጫ ሒደቶችን እጅግ በጣም ባጠረ ጊዜእና እያንዳንዱን ወደ ቀጣዮቹ መሸጋገር ከመጀመሩ በፊት መጠናቀቅ ያለበትን ሁኔታ ግምት ውስጥ ማስገባት ይኖርበታል፡፡[56] የምርጫ ክርክሮችን ተመልክቶ ውሰኔ የሚሰጠው አካል የሚቀርቡትን ቅሬታዎችን በትክክል ለመፍታት እንዲያስችል በሚቀመጠው አጭር የጊዜ ገደብ እና ቅሬታው የቀረበበት ሰው ወይም አካል የመከላከል መብት እና አስፈላጊ በሆኑ ጉዳዮች መካከል ሚዛናዊ መሆን አለበት፡፡[57] በተጨማሪም

---

[54] **የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር** 27፣ገጽ 22see also Barry H. Weinberg, The Resolution of Election Disputes: Legal Principles that Control Election Challenges, 2nd Edition, 2005, pp.25

[55] ዝኒ ከማሁ

[56] ዝኒ ከማሁ

[57] Parliamentary Assembly of the Council of Europe, Resolving Election Disputes in the OSCE Area: Towards a Standard Election Dispute Monitoring System, 2000, pp.

በአጠቃላይ የተከሰቱትን ቅሬታዎች ለመፍታት አጭር ጊዜ ማቅረቡ ጤናማ የሕግ አሠራር ነው፡፡

ብዙ የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓቶች በሕግ በተወሰነ ጊዜ ውስጥ በጊዜው ያልተሟገቱትን ሁሉንም ድርጊቶች እና የምርጫ አስፈፃሚ ውሳኔዎች የማይሻሩ መርህን ይከተላሉ፡፡[58] አንድ የተወሰነ የምርጫ ቅሬታ ላይ የሚሰጥን ውሳኔ ጊዜው ካለፈ በኂላ ባለው ደረጃ ትክክለኛነት ላይ ጥያቄ ለማቅረብ የማይቻል ያደርገዋል፡፡ ለምሳሌ እንደ ሜክሲኮ ባሉአገሮች በምርጫ ቅስቀሳ ወቅት የተፈፀመ ሕገ-ወጥ ድርጊት በተጎዳው ሰው ወይም በፓርቲውተቃውሞ ካልቀረበ በቀርውጤቱ በሚገለጽበት መድረክ ላይ ምርጫውን ለመሰረዝ ምክንያት ሆኖ ቢነሳ በሕግ አይፈቀድም፡፡[59]

ይህ መርህ የሚሠራው ሕገ-ወጥነትን በወቅቱ ለመቃወም ሲቻል ብቻ መሆኑን ልብ ሊባል ይገባል፡፡ ቅሬታው በተነሳበት ጊዜ ቅሬታውን ለማሰማት የሚያስችል ስርዓት ካልተቀመጠ ውጤቱ ይፋ ሲሆን መቃወም መቻሉ ተገቢ ነው ተብሎ የሚታሰብበት ምክንያት ሊኖር ይችላል፡፡[60] ስለሆነም በጥቅሉየምርጫ ሕጎች ሲወጡ ለሚነሱ የምርጫ ቅሬታዎች መፍትሄ ለመስጠት የሚያስችል ልዩ እና ስልታዊ ቀነ-ገደቦችን ማስቀመጥ መቻል አለባቸው፡፡

[58]ዝኒ ከማሁ
[59]ዝኒ ከማሁ
[60]ዝኒ ከማሁ

## ሠ) የመደመጥ መብትን የጠበቀ መሆን

የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት የመደመጥ መብት እንዲሁም መከላከያ ማስረጃ የማቅረብመብትን ለቅሬታ አቅራቢውም ሆነ ቅሬታ ለቀረበበት አካል ማረጋገጥ ይገባዋል፡፡[61] ይህም ግራቀኙ ክርክራቸውን የማቅረብ እድልን መጎናጸፍና የምርጫ ክርክርን ለመመልከት ስልጣን ያለው አካል የቀረበለትን ቅሬታ ተመልክቶ ተገቢ ውሰኔ መስጠትን ያካትታል፡፡[62]

የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት የቀረቡትን ቅሬታዎች የሚደግፉ ወይም የሚቃወሙ ማስረጃዎች በሁሉም ወገኖች ለጉዳዩ መቅረባቸውን ማረጋገጥ መቻል አለበት እንዲሁምይህንን የቀረቡትን ማስረጃዎች መዝኖ የተገለጸው ፍሬ ነገር ለምን ውድቅ እንደተደረገ ወይም ተቀባይነት እንዳገኘ ማረጋገጥ የሚያስችል መሆን አለበት፡፡[63] በጠቅላላው ሁሉም ስነ-ሥርዓታዊ ሂደቶች የሁሉንም ወገኖች የእኩልነት መብት በጠበቀ መንገድ መመራት አለባቸው፡፡

የምርጫ ህግ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ተቀባይነት እንዲኖራቸው ቅሬታዎችን ማን ማቅረብ እንደሚችልና ህጋዊ እውቅና እንዳለው መስፈርቶቹን በግልፅ ማስቀመጥ አለበት፡፡እንዲሁም የምርጫ ክርክርን የሚመለከተው አካል የቀረበው ቅሬታ ተቀባይነት ያለው ነው ወይስ አይደለም በሚለው ላይ

[61] African Union Panel of the Wise, "Election-Related Disputes and Political Violence: Strengthening the Role of the African Union in Preventing, Managing, and Resolving Conflict," The African Union Series, New York: International Peace Institute, July 2010.

[62] The International Foundation for Electoral Systems, Bench Book on electoral dispute resolution 2nd edition, pp.24

[63] ዝኒ ከማሁ

ውሳኔውን ለሁሉም ለሚመለከታቸው አካላት በጽሁፍ ማሳወቅ አለበት፡፡ ከዚህ በተጨማሪም ምክንያቶቹ ግልጽ የሆኑና በበቂ አመክንዮ የተደገፉ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡[64]

የምርጫ ህግ የምርጫውን ውጤት በመቃወም ለሚቀርብ ቅሬታ የትኛዎቹ የህግ መፍትሄዎች ሊሰጡ እንደሚችሉ በግልፅ ማስቀመጥ አለበት፡፡ በተለይም አጠቃላይ ወይም ከፊል እንደገና ቆጠራ እንዲታዘዝ ወይም የምርጫውን ውጤት ሙሉ በሙሉ ወይም በከፊል ውድቅ ለማድረግ የሚያስፈልጉትን ስልቶች ፣ ልዩ ምክንያቶች እና ማስረጃዎች መግለጽ እና የትኛው የምርጫ ክርክርን የሚመለከተው አካል የመወሰን ስልጣን እንዳለው መግለፅ አለበት፡፡[65]

## ረ) ፍርድ እና ውሳኔዎች ተፈጻሚ የሚሆኑበት ሂደት መኖር

የምርጫ ክርክርን ለመመልከት ስልጣን ያለው አካል መርምሮ የሚሰጣቸው ውሰኔዎች ጊዜውን ጠብቀው ሙሉ በሙሉ መፈጸም መቻላቸው ለምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓቱ መጎልበት ትልቅ ሚና አለው፡፡[66] የምርጫ ክርክርን ለመመልከት ስልጣን ያለው አካል የሚሰጣቸውን ውሳኔዎች ማስፈጸም የህዝብ ፖሊሲ ጥያቄ ሲሆን ሁሉም ባለስልጣናት ለዚህ ውሳኔ የተሟላ ተፈጻሚነት የበኩላቸውን አስተዋፅዖ የማድረግ ግዴታ አለባቸው፡፡ የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት አንድ

[64] ዝኒ ከማሁ
[65] ዝኒ ከማሁ
[66] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 35፣ገጽ 9

የፖለቲካ ድርጅት ወይም ዜጋ በአንድ ጉዳይ ላይ ያቀረበውን ቅሬታ ትክክል መሆኑን አምኖ ተቀብሎ የሚሰጠው ውሳኔ እና መፍትሄ ጊዜውን ጠብቆ ሙሉ በሙሉ ተፈጻሚ የሚሆንበትን ሂደት የማያረጋግጥ ከሆነ ውሳኔ መሰጠቱ ፋይዳ አይኖረውም፡፡

በምርጫ ክርክር ውስጥ የሚሰጡ ውሳኔዎች ወይም ፍርዶች ከተሰጡ በኋላ ሙሉ በሙሉ ተግባራዊ ለማድረግ ህግና ደንቦች መከበር አለባቸው፡፡[67] ለምሳሌ ግዴታው የአንድን ተግባር መፈጸም ሲያካትት በዚህ ግዴታ ውስጥ ያለ ሰው ወይም አካል እንደየ ሁኔታው ይህን ለማድረግ ተጨባጭ የጊዜ ገደብ ሊቀመጥለት ይገባል፡፡ ይህ የጊዜ ገደብ በፍርዶች ወይም ውሳኔዎች ውስጥ መቀመጥ አለበት፡፡ ይህ ጊዜ ካለፈ በኋላ ድርጊቱ ካልተፈፀመ ፣ የምርጫ ክርክሩን የተመለከተው አካል ግለሰቡን ወይም ተቋሙን በትዓዛዙ አግባብ እንዲፈጽም ለማስገደድ ተገቢ እርምጃዎችን እንዲወስድ ሥልጣን ሊሰጠው ይገባል፡፡[68]

### ሰ) በምርጫ ሕጎች አተረጓጎም እና አተገባበር ላይ ወጥነት መኖር

የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓቱ ነፃና ገለልተኛ ስለመሆኑ አንዱ ማሳያ ተደርጎ የሚወሰደው የተለያዩ የፖለቲካ ጫናዎች ቢኖሩም በሕገ መንግሥት፣ በሕግ፣ በሥርዓት እና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ምርጫን የተመለከቱ ዓለም አቀፍ ድንጋጌዎች በመተርጎም እና በመተግበሩ ላይ

---

[67] Parliamentary Assembly of the Council of Europe, Handbook for the Observation of Election Dispute Resolution, 2019, pp.38

[68] ዝኒ ከማሁ

ያለው ወጥነት ሲረጋገጥ ነው፡፡[69] እንዲሁም የነባራዊ ሁኔታዎች ተለዋዋጭ መሆንን መሰረት አድርጎ ተፈፃሚነት ባላቸው የምርጫ ድንጋጌዎች ላይ አዳዲስ ግንዛቤዎችና የአተረጓጎም ለውጥ የሚጠይቁ በሚሆኑበት ሰዓት፣ ለውጦቹ ሙሉ በሙሉ ትክክል መሆናቸውን ለማረጋገጥ ልዩ ጥንቃቄ መደረግ አለበት፡፡[70] በዋናነት ደግሞ የምርጫን ክርክር እንዲመለከቱ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የሚሰጡት ውሳኔም ሆነ ትዓዛዛት ተገማች መሆን መቻላቸው ለህጋዊ እርግጠኝነት እና ለምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓቱ ታማኝነት መሰረታዊ ጉዳይ ነው፡፡[71] በአጠቃላይ የትኛውም የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ተፈጻሚ የሚደረጉትን ህገ-መንግስታዊና ህጋዊ ድንጋጌዎችን ወጥነት ባለው መልኩ ለመተርጎም እና የህግ ክፍተቶችን ለመሙላት ያስችለው ዘንድ ግልፅ እና ወጥ መስፈርቶችን በማዘጋጀት ጥረት ማድረግ ይኖርበታል፡፡[72]

### 1.4. የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት አይነቶች

የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት በምርጫ ሂደት ውስጥ ወይም ከምርጫው በኋላ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመፍታት እንዲያስችሉ የተቀመጡ ዘዴዎች ናቸው፡፡ እነዚህ ስርዓቶች የሚነደፉት የምርጫው ሂደት ግልፅ ፣ ፍትሃዊ እና ተዓማኒ እንዲሆን እንዲሁም የምርጫው

[69]ዝኒ ከማሁ
[70]ዝኒ ከማሁ
[71] International Foundation for Electoral System, Guidelines for Understanding, Adjudicating, and Resolving Disputes in Elections, 201, pp. 50see also, Parliamentary Assembly of the Council of Europe, Handbook for the Observation of Election Dispute Resolution, 2019
[72]International Foundation for Electoral System, When Are Elections Good Enough? Validating or Annulling Election Results, 2018

ውጤት በሁሉም ባለድርሻ አካላት ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው ለማድረግ ነው።[73] ከዚህ ጋር በተገናኘ በአለም አቀፍ ደረጃ በርካታ ዓይነት የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓቶች ያሉ ሲሆን እነሱንም ከዚህ በታች አንድ በአንድ እንመለከታቸዋለን።

### 1.4.1. የምርጫ ክርክሮች በህግ አውጪው ምክር ቤት ወይም በሌላ የፖለቲካ አካል የሚፈታበት ስርዓት

ይህ በጣም ጥንታዊ የሆነ የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት አይነት ነው።[74] ይህ ስርዓት በምርጫ ወቅት የሚነሱ ክርክሮችን አይቶ የመጨረሻ እልባት እንዲሰጥ ለህግ አውጭ አካል ወይም ለሌላ የፖለቲካ አካል የሚሰጥ ሲሆን ህግ አውጪው አካል ማንኛውንም ክርክሮችን ጨምሮ በምርጫ ትክክለኛነት ላይ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን አለው።[75]በፈረንሣይ የህግ ስርዓት ይህ 'የስልጣን ማረጋገጫ' እና በአሜሪካ የህግ ስርዓት 'የምርጫ መመዘኛ ወይም ማረጋገጫ' ተብሎ ይጠራል።[76] ይህን አይነቱን የምርጫ ክርክሮች መፍቻ ስርዓት በብዛት ጥቅም ላይ ሲያውሉት የሚስተዋለው ፓርላሜንታዊ የመንግሥት ሥርዓት ባለባቸው አገሮች ሲሆን ሕግ አውጪው በምርጫ ሂደት ውስጥ ትልቅ ሚና ይኖረዋል ማለት ነው።[77] በመሆኑም የምርጫ ክርክሮችን እንዲመለከት ስልጣን የተሰጠውይህ የህግ አውጪ ምክር ቤት ምስክር የመጥራት፣

[73]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 18፣ገጽ 12-14
[74]ዝኒ ከማሁ
[75]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11፣ገጽ 20
[76]ዝኒ ከማሁ
[77]ዝኒ ከማሁ

ማስረጃን የመመዘንእና በክርክር ላይ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ይኖረዋል ማለት ነው፡፡[78]

ከዚህ ጋር በተያያዘ የምርጫ ክርክርን እንዲፈታ ለህግ አውጭ ምክር ቤት የሚሰጥበት ታሪካዊ ምክንያት በስልጣን ክፍፍል መርህ ላይ የተመሰረተ ነው፡፡[79] በዚህ መሰረት እያንዳንዱ የመንግስት አካል ከሌላው አካል የፀዳ ስለሆነ የሌሎችን ስብጥር በሚነካ ውሳኔ ውስጥ መሳተፍ የለበትም ከሚል ሃሳብ የተነሳ ነው፡፡[80] በተጨማሪም የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ለህግ አውጭው አካል መስጠትን የሚደግፉ ወገኖች የአብዛኛውን የፍትህ አካላት ዲሞክራሲያዊ ያልሆነ ባህሪ በማንሳት የነዚህ አካላት ውሳኔ ከህግ አውጭው አካል ውሳኔ የበላይ መሆን የለበትም ሲሉ ይከራከራሉ፡፡[81]

እንደዚህ አይነቱ የምርጫ ክርክሮችን በምክር ቤት የሚፈቱበት ስርዓት የተለያዩ ጠቀሜታዎች ያሉት ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ አንዱ እያንዳንዱ የሚነሱ የምርጫ ክርክሮችየበለጠ ፖለቲካዊ ትኩረት እንዲያገኙ የሚያደርግ ሲሆን ይህም አለመግባባቱ ከሰፋፊ ፖለቲካዊ ጉዳዮች ጋር በተገናኘ ጊዜ የበለጠ ትኩረት እንዲያገኙ ያስችላል፡፡ በተጨማሪም የምክር ቤት የክርክር አፈታት ስርዓት ለፖለቲካ ፓርቲዎች እና እጩዎች

[78]ዝኒ ከማሁ
[79]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 18፣ገጽ 12-14
[80]ዝኒ ከማሁ
[81]ዝኒ ከማሁ

በጨዋታው ውስጥ ስላለው የፖለቲካ እንቅስቃሴ የበለጠ ግንዛቤ ሊኖራቸው ስለሚችል የበለጠ ተደራሽነት እንዲኖር ያስችላል፡፡[82]

ሆኖም ግን በምክር ቤት የክርክር አፈታት ሥርዓት ላይም እንደ ደካማ ጎን የሚነሱ ትችቶች አሉ፡፡ ከነዚህውስጥም አንደኛው ስጋት በተለይ ገዥው ፓርቲ በህግ አውጭው ውስጥ አብላጫውን ወንበር ሲይዝ ለፖለቲካ ተጽእኖ ሊዳረጉ ይችላሉ የሚል ነው፡፡ በተጨማሪም የምክር ቤት የክርክር አፈታት ስርዓቶች የዳኝነት ወይም የአስተዳደር ስርዓት የህግ እውቀት ወይም የሚከተሉት ሥነ-ስረዓታዊ ጥበቃዎች ላይኖራቸው ስለሚችል ይህም ወደ ወጥነት የለሽ ወይም ፍትሃዊ ወዳልሆነ ውሳኔዎች ሊያመራ ይችላል፡፡[83] በአጠቃላይ የምክር ቤት የክርክር አፈታት ሥርዓት ውጤታማነት በተመረጠው የምክር ቤት ኮሚቴ ነፃ እና ገለልተኝነት ደረጃ ላይ የተመሰረተ ነው የሚሆነው፡፡

### 1.4.2. የምርጫ ክርክሮች በዳኝነት አካሉ የሚፈቱበት ስርዓት

የምርጫ ክርክርን የመዳኘት ስልጣኑን ለዳኝነት አካሉ መሰጠት አለበት በማለት የሚያነሱ አካላት ምርጫን የመዳኘት እና የማረጋገጥ ተግባር በመሠረቱ ተፈጥሮዊ የዳኝነት ባህሪ ያለው ነው በማለት ነው፡፡[84] ከዚህ በተጨማሪ ምርጫው ነፃ ፣ ፍትሃዊ ፣ እውነተኛ እና ትክክለኛ እንዲሆን ለማድረግ ያስችል ዘንድ የምርጫ ክርክሮችን የመዳኘት ስልጣኑ ለዳኝነት

[82]ዝኒ ከማሁ
[83]ዝኒ ከማሁ
[84]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11፣ገጽ 21

አካል ሊሰጥ ይገባል በማለት ያነሳሉ፡፡[85] በዋናነት ደግሞ የምርጫ ክርክሮችን የመፍታት ስልጣን ለመስጠት ህገ መንግስታዊነትን፣ ህጋዊነትን፣ የህግ የበላይነትን ፣ መሰረት በማድረግ ነው እንጂ ከፖለቲካዊ ጥቅም ጋር በማገናዘብ ላይ የተመሰረተ መሆን የለበትም በማለት ያነሳሉ፡፡[86] በእንዲህ አይነቱ ስርዓት ከምርጫ ጋር በተገናኘ የሚነሱ ክርክሮች በፍርድ ቤት መፍትሄ እንዲያገኙ ይደረጋል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ ክርክሮች በፍርድ ቤት የሚፈቱበት ስርዓት ጠንካራና ገለልተኛ የዳኝነት ሥርዓት ባለባቸው አገሮች ጥቅም ላይ ሲውል ይስተዋላል፡፡ ይህም ፍርድ ቤቶች ሕግን መሠረት አድርገው ገለልተኛ በሆነ መንገድ ውሳኔ እንደሚሰጡ ስለሚታመን ነው፡፡[87] በእንደዚህ ያለው ስርዓት ክርክሮች ህጋዊ ሂደትን ተከትሎ እንዲፈቱ የሚያስችል ሲሆን ተከራካሪ ወገኖችም ክርክሮቻቸውንና ማስረጃዎቻቸውን በችሎት ፊት እንዲያቀርቡ እድል የሚሰጥ ነው፡፡ እንዲሁም የእንደዚህ አይነቱ ስርዓት አንዱ ጥቅም ክርክሮች ከሌሎች የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓቶች የበለጠ ነፃ እና ገለልተኛ በሆነ አካል እንዲፈቱ ማስቻላቸው ነው፡፡ ይህም የሚመነጨው ዳኞች ከፖለቲካዊ ጉዳዮች ወይም ሌሎች ጉዳዮች ይልቅ ህጉንና ማስረጃውን ብቻ መሰረት አድርገው ውሳኔ እንዲሰጡ የሚጠበቅባቸው የሰለጠኑ የህግ ባለሙያዎች በመሆናቸው ነው፡፡[88] በተጨማሪም ክርክሮች በፍርድ ቤት የሚፈቱበት ስርዓት በሚሰጠው

[85]ዝኒ ከማሁ
[86]ዝኒ ከማሁ
[87]ዝኒ ከማሁ
[88]ዝኒ ከማሁ

ውሳኔ የበለጠ እርግጠኝነት እና ተገማችነት ያላቸው ናቸው፡፡ ምክንያቱም በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሳኔዎች በተለምዶ አስገዳጅ እና በአገሪቱ የህግ ስርዓት ውስጥ ተፈጻሚነት ያላቸው በመሆናቸው ነው፡፡ ይህም ህዝቡ በምርጫ ሂደቱ ላይ ያለውን እምነት ከፍ ሊያደርግ እና መረጋጋትን እና ህጋዊነትን ሊያጎለብት ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡[89]

ይሁን እንጂ ክርክሮች በፍርድ ቤት የሚፈቱበት ስርዓት ላይ ሲነሱ የሚስተዋሉ ችግሮችም በዛው ልክ አሉ፡፡ ከእነዚህ ውስጥም የመጀመሪያው ይህ አይነቱ ስርዓት ከሌሎች የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓቶች በበለጠ ቀርፋፋ እና ውድ ሊሆንመቻሉ ነው፡፡ይህም የውጤት መዘግየቶችን ሊፈጥር ይችላል፡፡[90] በተጨማሪም ክርክሮች በፍርድ ቤት የሚፈቱበት ስርዓት ልዩና ከፍ ያለ የህግ እውቀት እንዲሁም ግብአቶችን መፈለጋቸው ነው፡፡ ይህም ለአንዳንድ ወገኖች የፍትህ ተደራሽነትን ሊገድብ የሚያስችል ውጤት ይኖረዋል፡፡ በአጠቃላይ ክርክሮች በፍርድ ቤት የሚፈቱበት ስርዓት ውጤታማነት የሚወሰነው ባለው የህግ ተርጓሚው አካል ጥንካሬ እና ጥራት ላይ ነው፡፡ የምርጫ ክርክሮች በፍትሃዊነትናበገለልተኝነት እንዲፈቱ እና የምርጫው ውጤት ህጋዊ ነው ተብሎ በሰፊው ህዝብ ተቀባይነት እንዲኖረው ጠንካራ እና ገለልተኛ የዳኝነት ስርዓት አስፈላጊ መሆን እንደሚገባው መዘንጋት የሌለበት ጉዳይ ነው፡፡

---

[89] ዝኒ ከማሁ

[90] ዝኒ ከማሁ

### 1.4.3. የምርጫ ክርክሮች በአስተዳደራዊ አካላት የሚፈቱበት ስርዓት

በዚህ አይነት የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት የምርጫ ክርክሮችን ተመልክቶ ውሳኔ እንዲሰጥ ሃላፊነት የሚሰጠው ነፃ ለሆነ የምርጫ አስተዳዳሪ አካል ነው፡፡[91] ይህም አካልየምርጫ ሂደቶችን የማደራጀት እና የማስተዳደር ሃላፊነት ከመውሰድ በተጨማሪ የምርጫ ክርክሮችን የመፍታት እና የምርጫ ሂደቱን ትክክለኛነት በተመለከተ የመጨረሻ ውሳኔ የመስጠት ስልጣን ይኖረዋል፡፡[92] እንዲህ አይነቱ ስርዓት በዋናነት በላቲን አሜሪካ ነው ጥቅም ላይ የሚውለው፡፡[93] በተጨማሪ ይህ ስርዓት የምርጫ ክርክሮችን በተለመደው መንገድ አከራክሮ የመወስን ስልጣን ብቻ ሳይሆን፤ የምርጫ ሂደቶችን ትክክለኛነት ጨምሮ የመጨረሻ ውሳኔዎችን ይሰጣል፡፡ እንዲሁም እነዚህን የሚሰጡ ውሳኔዎች ማንኛውም የፍትህ ፣ የአስተዳደር ወይም የሕግ አውጭ አካል ለመመልከትና ለመገምገም አይችልም፡፡[94] ከዚህ ጋር በተገናኘ የምርጫ አስተዳዳሪ አካሉ ነፃ እና ገለልተኛ ነው ተብሎ በሚታሰብባቸው እና ክርክሮችን በጊዜ እንዲሁም ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፍታት የሚያስችል የህግ እውቀት እና ግብአት ባለባቸው ሀገራት ከፊል የዳኝነት ስልጣን ባለው የምርጫ አስተዳደራዊ አካል መመልከቱ

[91] Resolving Election Disputes in the OSCE Area: Towards a Standard Election Dispute Monitoring System, OSCE/ODIHR, Warsaw, 2000. See also Code of Good Practice in Electoral Matters (Venice Commission's Code of Good Practice), The Council of Europe, Venice, 2002 See also Inter-Parliamentary Union's Declaration on Criteria for Free and Fair Elections, 1994, Paragraph 4 (9).

[92]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11፣ገጽ 22

[93]ዝኒ ከማሁ

[94]ዝኒ ከማሁ

የተለመደ ተግባር ነው፡፡[95] በእንደዚህ ያለ ስርዓት ውስጥ ክርክሮች በአስተዳደራዊ ሂደት ይፈታሉ፤ ተከራካሪ ወገኖችም በምርጫ ኮሚሽኑ ፊት ማስረጃዎችን እና ክርክሮችን እንዲያቀርቡ ይደረጋል፡፡[96]

ከዚህ ጋር በተገናኘ እንደዚህ አይነቱ የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት አንዱ ጥቅማቸው ከፍ ያለ ነፃነትና ገለልተኝነትን በጠበቀ መልኩ ቀልጣፋና ተደራሽ አማራጭ ማቅረብ መቻላቸው ነው፡፡[97] በተጨማሪም ከፊል የዳኝነት ስልጣን ባለው አስተዳደራዊ አካል ክርክሮች እልባት የሚያገኙበት ስርዓት የበለጠ ልዩ እና በምርጫ ሂደት ውስጥ ስላለው ውስብስብነት የበለጠ ግንዛቤ ሊኖራቸው ይችላል፡፡ ይህም የበለጠ በመረጃ የተደገፈ እና ውጤታማ ውሳኔዎችን ያመጣል ተብሎ ይታሰባል፡፡[98] ይሁን እንጂ ቅሉ በእንዲህ አይነቱ የምርጫ ክርክሮች አፈታት ስርዓት ላይ የሚነሱም ችግሮች አሉ፡፡ ከእነዚህም ውስጥ በቀዳሚነት የሚነሳው ጉዳይ ጠለቅ ያለ የህግ እውቀት እና የሥርዓት ጥበቃዎች ሊጎድላቸው ይችላል የሚል ነው፡፡ ይህም ወጥነት ወደሌለው የክርክር ዘይቤ በማምራት ፍትሃዊ ያልሆኑ ውሳኔዎች እንዲፈጠሩ ሊያደርግ ይችላል ተብሎ ይታሰባል፡፡[99] በተጨማሪም ከፊል የዳኝነት ስልጣን ባለው አስተዳደራዊ አካል ስርዓት በተለይም ገዥው ፓርቲ በምርጫ ኮሚሽኑ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ በሚያሳድርበት ጊዜ ለፖለቲካዊ ተጽእኖ ወይም ማጭበርበር ሊጋለጥ

[95] ዝኒ ከማሁ
[96] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 11፣ገጽ 20
[97] ዝኒ ከማሁ
[98] ዝኒ ከማሁ
[99] ዝኒ ከማሁ

ይችላል፡፡[100] በአጠቃላይ ከፊል የዳኝነት ስልጣን ባለው አስተዳደራዊ አካል የምርጫ ክርክሮች አፈታት ሥርዓት ውጤታማነት የሚወሰነው በምርጫ ኮሚሽኑ የነጻነት እና የገለልተኝነት ደረጃ ልክ ነው፡፡ አለመግባባቶች በፍትሃዊ እና በገለልተኝነት እንዲፈቱ እና የምርጫው ውጤት ህጋዊ ነው ተብሎ በሰፊው ተቀባይነት እንዲኖረው የዳኝነት ስልጣን ያለው ጠንካራ እና ገለልተኛ የአስተዳደር አካል አስፈላጊ ነው፡፡

### 1.4.4. የምርጫ ክርክሮች በጊዜያዊነት በሚቋቋሙ አካላት የሚፈቱበት ስርዓት

የምርጫ ክርክሮች የሚፈቱበት ስርዓት የምርጫውን ትክክለኛነት እና ፍትሃዊነት ለማረጋገጥ ወሳኝ ሚና አላቸው፡፡ እንደዚሁ ሁሉ የዚህ አይነቱ የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ባህሪ የምርጫ ክርክሮችን ተመልክቶ መፍትሄ የሚሰጠው አካል በጊዜያዊነት የሚቋቋም ነው፡፡[101] ይህ ማለትም የምርጫ ክርክሩን የሚመለከተው አካል የሚቋቋመው ለአንድ የምርጫ ጊዜ ወይም ምናልባትም ከአንድ በላይ ለሆኑ የምርጫ ጊዜያት ሊሆን ይችላል፡፡ ነገር ግን ተግባራዊ የሚደረገው ቋሚ የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት እስኪፈጠር ድረስ እንደመሸጋገሪያ እርምጃ ነው፡፡[102]

[100]ዝኒ ከማሁ
[101]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 18
[102]ዝኒ ከማሁ

ይህ በጊዜያዊነት የሚቋቋመው አካልም እንደ ዳኞች ፣ ጠበቆች ፣ ምሁራን እና ሌሎች በምርጫ ህግ እና አሰራር ላይ ያሉ ባለሙያዎችን ያቀፈ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን እንደየ ምርጫው ልዩ ሁኔታ እና እንደየ ህግ ማዕቀፉ የሚመለከቱት አካላት ስብጥር ሊለያይ መቻሉን ልብ ሊባል ይገባል። የምርጫ ክርክሮችን የሚመለከቱት ጊዜያዊ አካላት ከምርጫው ጋር በተያያዙ ቅሬታዎችን መቀበል እና መፈተሽ ፣ የምርጫ ህጎችን እና የአሰራር ሂደቶችን መጣስን መመርመር እና በምርጫው ውጤት ትክክለኛነት ላይ ውሳኔ መስጠትን ያጠቃልላል። እንዲሁም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በድጋሚ ቆጠራን የማዘዝ ፣ ውጤቱን የመሻር ወይም አዲስ ምርጫ እንዲከናወን ስልጣን ሊኖራቸው ይችላል።[103] ከዚህ ጋር በተገናኘ የዚህ አይነቱ የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት አንዱ ጥቅም ለአንድ የተወሰነ ሁኔታ ምላሽ ለመስጠት ፍጥነት ሊታከልበት ይችላል የሚል ነው። ይህም የምርጫ ክርክሮችን ወቅታዊ እና ውጤታማ በሆነ መንገድ ለመፍታት ይረዳል።[104]ይሁን እንጂ ቅሉ የምርጫ ክርክሩን የሚመለከቱት አካላት የሚሰጡት ውሳኔ ተአማኒነት እና ህጋዊነት በተለያዩ ሁኔታዎች ላይ የተመሰረተ ነው። ለምሳሌ በአባላቱ ገለልተኛነት እና እውቀት ፣ የአሠራሩ ግልጽነት እና አሠራሩን የሚመራ የህግ ማዕቀፍ በጥቂቱ ተጠቃሽ ናቸው።[105]

[103]ዝኒ ከማሁ
[104]ዝኒ ከማሁ
[105]ዝኒ ከማሁ

## 2. የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት በኢትዮጵያ

ኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድን ፣የክልልና የፌዴራል ፍርድ ቤቶችን እና የፌዴሬሽን ምክር ቤትን ያካተተ ባለ ብዙ ደረጃ የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት አላት፡፡[106] ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ ከምርጫ ሒደቱ ጋር ተያይዘው የሚነሱ አለመግባባቶችን የመፍታት ኃላፊነት አለበት፡፡[107] እንዲሁም የክልል እና የፌደራል ፍርድ ቤቶች በበኩላቸው በይግባኝና በመጀመሪያ ደረጃ በምርጫ ክርክሮች ላይ የዳኝነት ስልጣን አላቸው፡፡[108] የፌዴሬሽንምክር ቤት እንዲሁ ከምርጫ ጋር በተያያዘ የሚነሱ የምርጫ ክርክሮች ህገ መንግስቱን በቀጥታ ተግባራዊ ከማድረግ በዘለለ የህገ መንግስት ትርጉም የሚያስፈልጋቸው ከሆነ የመጨረሻ ተርጓሚ አካል ሆኖ ያገለግላል፡፡[109] ስለሆነም በዚህ ክፍል ውስጥ በኢትዮጵያ የምርጫ ክርክሮች አፈታትን በተመለከተ ተፈጻሚነት ያላቸውን የህግ ማዕቀፎች ለመመልከት ይሞከራል፡፡

### 2.1. የምርጫ ክርክር አፈታት የህግ ማዕቀፎች

የምርጫ ክርክሮች የሚፈቱበት ስርዓትና የህግ ማዕቀፎች እንደየ ሀገራቱ የህግ ስርዓቶቻቸው ይለያያሉ፡፡ ኢትዮጵያ የምርጫ ክርክሮችን ለመፍታት

---

[106]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 3፣ በተጨማሪ የኢትዮጵያ የምርጫ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ፣1162/2011፣ የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ፣1133/2011 ይመልከቱ፡፡

[107]የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ፣1133/2011፣አንቀጽ 7፡፡

[108]የኢትዮጵያ የምርጫ፣የፖለቲካ ፓርቲዎች የምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባርአዋጅ፣1162/2011፣አንቀጽ 153-158

[109]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 2

የሚያስችል የህግ ማዕቀፍ አላት። ከእነዚህም ውስጠ በዋናነት የኢፌድሪ ህገ መንግስት ለምርጫ ሕጋዊ መሠረት ያስቀመጠ ፣ የዴሞክራሲና የምርጫ መብቶች መሠረታዊ መርሆዎችን ያካተተ ፣ ነጻና ገለልተኛ የሆኑ ፍርድ ቤቶች እንዲቋቋሙ የደነገገ ፣ የመምረጥ መብትን እና የመመረጥ መብትን ያቀፈ እንዲሁም ምርጫን የማደራጀት እና የማካሄድ ኃላፊነት ያለበትን የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ነጻና ገለልተኛ ሆኖ ስራውን እንደሚያከናውን መሰረት የሚጥል ሆኖ እናገኘዋለን።[110] ከዚህ በተጨማሪ የወንጀል ህጉ በአምስተኛ ርእሱ ስር ምርጫን የሚመለከቱ ወንጀሎች ከአንቀጽ 466 እስከ 476 የተለያዩ የምርጫ ነክ ወንጀሎችን በመዘርዘር ያስቀምጣል።[111] ከዚህ ጋር በተያያዘ እንዲሁ ከምርጫ ጋር በተያያዙ የወንጀል ጉዳዮች ምርመራ እና የፍርድ ሂደት ላይ ፖሊስና ዐቃቤ ህግ የሚጠቀሙት ይህንንህግ ነው። ከሥነ-ምግባር ጥሰቶች በስተቀር ከምርጫ ጋር የተያያዙ የወንጀል ጥፋቶች በፖሊስና ዐ/ህግ የሚታዩ ሲሆን፣ በዚህም ረገድ የወንጀል ሥነ- ስርዓት ህጉ ድንጋጌዎችና ስነ ስርዓቶች ተፈፃሚ ይሆናሉ።[112] ስለሆነም ይህ እንዳለ ሆኖ ከዚህ በታች ባለው ክፍል ከምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ጋር በቀጥታ ግንኙነት ያላቸውን ህጎች በጥልቀት እንመለከታለን።

[110] ዝኒ ከማሁ
[111] የኢትዮጵያ ወንጀል ህግ፣414/2004፣ከአንቀጽ 466 እስከ 476
[112] የኢትዮጵያ የወንጀለኛ መቅጫ ስነ-ሥርዓት ህግ፣185/1954

### 2.1.1. የኢትዮጵያ የምርጫ ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የምዝገባና የምርጫ ሥነ-ምግባር አዋጅ[113]

በምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 የተደረጉት ማሻሻያዎች እንደተጠበቁ ሆነው ይህ አዋጅበዋናነት በጊዜው የወጣው ሁሉም ኢትዮጵያዊ በሚስጥራዊ የድምፅ አሰጣጥ ስርዓት ድምፁን በነፃ ፈቃዱ የሚሰጥበት እንዲሁም ህዝብ በእኩልነት በየደረጃው በሚካሄዱ ሁሉን አቀፍ ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ምርጫዎች ውስጥ እንዲሳተፉ ለማረጋገጥ ነው፡፡[114] ይህ የምርጫ አዋጅ ምርጫ ቦርድን በገለልተኛነት በማዋቀር ምርጫን የማደራጀት እና የማካሄድ ፣ የመራጮች ምዝገባ ፣ የእጩዎች ጥቆማ ፣ የምርጫ ቅስቀሳ እና ድምጽ አሰጣጥ ሂደቶችን በዝርዝር አስቀምጧል፡፡[115] ከዚህ በተጨማሪ ይህ አዋጅ አጠቃላይ የምርጫ ሂደቱን እና የፖለቲካ ፓርቲዎችን ምዝገባ ያስተዳድራል፡፡ እንዲሁም የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብና መርሆዎችን ያስቀምጣል፡፡ በዋናነት ደግሞ ማንኛውም የምርጫ እንቅስቃሴ አለም አቀፍ የምርጫ መስፈርቶችን በሚያሟላ የምርጫ ሂደት

[113] የምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 በቅርቡ ሁለት ማሻሻያ የተደረገበት ሲሆን በአዋጅ ቁጥር 1235/2013 ከኮሮና ጋር በተያያዘ ለስድስተኛው ምርጫ ብቻ ተፈጻሚ የሚሆን እጩዎች ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤትም ሆነ ለክልል ምክር ቤት ሲወዳደሩ የሚያቀርቡትን የድጋፍ ፊርማ መጠን ዝቅ የሚያደርግ ማሻሻያ ሲሆን ሌላው አዋጅ ቁጥር 1332/2016 በበኩሉ አንድ የፖለቲካ ቡድን ሃይልን መሰረት ያደረገ የአመጽ ተግባር ላይ የተሳተፈ እንደሆነና ይህን ተግባር ማቆሙንና ህገመንግስታዊ ዲሞክራሲያዊ ስርዓቱን አክብሮ ለመንቀሳቀስ መስማማቱን ከሚመለከተው የመንግስት አካል ከተረጋገጠ ፓርቲውበ ድጋሚ ሊመዘገብ እንደሚችል የሚገልጽ ነው፡፡ ነገር ግን የተደረጉት ማሻሻያዎች በዚህ ጽሁፍ ከተያዘው ጉዳይ ጋር ግንኙነት የሌላቸው በመሆኑ ስለማሻሻያዎቹ በዚህ ክፍል ውስጥ የምንመለከት አይሆንም፡፡

[114] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 108

[115] ዝኒ ከማሁ

መመራቱን የማረጋገጥ አላማ አንግቧል፡፡ እንዲሁም የፖለቲካ ፓርቲዎችን የሚያቋቁሙ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ አባል የሚሆኑ ዜጎችን መብቶችና ግዴታዎች ይደነግጋል፣ ፓርቲዎች የህግ ሰውነት የሚያገኙበትን አሰራር ይወስናል፡፡ እንዲሁም ፓርቲዎች እንደ ድርጅት በሚያከናውኗቸው ተግባራት ላይ ሊከተሏቸው የሚገቡ መሰረታዊ መርሆዎችን ያስቀምጣል፡፡ የፖለቲካ ፓርቲዎች ውህደትና ግንባሮች መመስረት ወይም ጥምረት መፍጠር የሚችሉበትን ስርዓት ያስተዳድራል፡፡ ምርጫ በሥነ-ምግባር እንዲመራና ነፃ፣ ሰላማዊ፣ ህጋዊ፣ ዲሞክራሲያዊና ታዓማኒ በሆነ መንገድ እንዲከናወን ፖለቲካ ፓርቲዎች፣ እጩዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲ አባላትና ደጋፊዎች በምርጫ ወቅት መከተል የሚገባቸውን የሥነ-ምግባር ደንቦች ያስቀምጣል፡፡[116] የምርጫ ክርክሮች ላይ አስተዳደራዊና ከፊል አስተዳደራዊ ውሳኔዎችን የሚሰጡ ተቋማትን ያቋቁማል፡፡[117]

### 2.1.2. የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ

ይህ አዋጅ የወጣው በህገ መንግስቱ አንቀፅ 102 መሰረት ነው፡፡[118] ይህ ህግ ምርጫ ቦርድ በተለያዩ ደረጃዎች ነፃ ፣ ፍትሃዊና ሰላማዊ ምርጫዎችን በማካሄድ ዜጎች በመረጧቸው ተወካዮች አማካኝነት የራስን በራስ የማስተዳደር መብታቸውን እንዲጠቀሙ የሚያደርግ ገለልተኛ የምርጫ አስፈጻሚ አካል ሆኖ እንዲያገለግል ስልጣን የሚሰጠው ህግ

[116] ዝኒከማሁ
[117] ዝኒከማሁ
[118] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 108

ነው፡፡[119] ይህንን በማድረጉም ምርጫ ቦርድ የኢትዮጵያን ዲሞክራሲ በማጠናከር ረገድ ወሳኝ ሚና እንዲጫወት ይረዳል፡፡ ምርጫ ቦርድ ተጠሪነቱ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሲሆን በክልሎች ቅርንጫፍ ጽ/ቤቶችን ሊከፍት ይችላል፡፡ የቦርዱም ስልጣንና ተግባራት በአዋጁ አንቀጽ 7 ስር በዝርዝር ተቀምጠዋል፡፡[120]

### 2.1.3. መመሪያዎች

የኢትዮጵያ ብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ሃላፊነቱን ለመወጣት የሚያስችሉ መመሪያዎችን እንዲያወጣ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀፅ 7(11) ላይ ስልጣን ተሰጥቶታል፡፡[121] በዚህ በህግ በተሰጠው ስልጣን መሰረት በርካታ መመሪያዎችን አውጥቷል፡፡ የምርጫ ክርክር አፈታት ሂደትን በተመለከተ ተፈፃሚነት የሚኖራቸው ዋና ዋና መመሪያዎች የምርጫ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች አደረጃጀትና አሰራር መመሪያ ፣ የመራጮች ምዝገባ መመሪያ ፣ የእጩዎች ምዝገባ፣ የድጋፍ ፊርማ አሰባሰብና የእጩዎች ምልክቶች አመራረጥ መመሪያ፣ የምርጫ ዘመቻ፣ ቅስቀሳ ሥነ-ምግባር መመሪያ እና የድምፅ አሰጣጥ፣ የድምፅ ቆጠራና የምርጫ ውጤቶች ይፋ አደራረግ መመሪያ ናቸው፡፡[122] በጠቅላላው እነዚህና ኢትዮጵያ ያፀደቀቻቸው አለም አቀፍ ስምምነቶች የምርጫ ክርክሮችን ለመፍታት ጥቅም ላይ የሚውሉ

[119] ዝኒ ከማሁ
[120] ዝኒ ከማሁ
[121] የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 107
[122] ዝኒ ከማሁ፣ በተጨማሪ የመራጮች ምዝገባ አፈጻጸም መመሪያ ቁጥር 6/2013፣የእጩ ተወዳዳሪዎች ምዝገባ፣ የድጋፍ ፊርማ አሰባሰብና የመለያ ምልክቶች አመራረጥ መመሪያ ቁጥር 7/2013 ይመልከቱ፡፡

የህግ ማዕቀፎች ናቸው፡፡ የኢትዮጵያ የምርጫ የሕግ ማዕቀፍ ሁሉን አቀፍ ቢሆንምግልጽ ያልሆነና ለትርጉም ክፍት እንዲሆን ተደርጎ የተቀረጸ በመሆኑ በምርጫ ሒደት የሚፈጠሩ ክርክሮችን እልባት ለመስጠት ተግዳሮት እየፈጠረ ይገኛል፡፡ ስለሆነም የምርጫ የህግ ማዕቀፎችን ለማጠናከር እና በምርጫው ሂደት ውስጥ የበለጠ ግልፅነትና ተጠያቂነት እንዲኖር ለማስቻል የህግ ማሻሻያዎች ሊደረጉ ይገባል፡፡

## 2.2. የምርጫ ክርክር አይነቶች በኢትዮጵያ

በምርጫ ሂደት የተለያዩ ደረጃዎች ውስጥ ሊነሱ የሚችሉ በርካታ የቅሬታ ፣ ክርክር እና የስነ-ምግባር ደንብ ጥሰት አይነቶች አሉ፡፡ እነዚህም በምርጫ ተወዳዳሪዎች መካከል፣ በምርጫ ተወዳዳሪዎች እና በምርጫ አስፈፃሚዎች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶችን፣ እንዲሁም ከምርጫ ዝግጅት ጋር የተያያዙ ጉዳዮች፣ ከአሰራርና ማስፈፀሚያ ዘዴ ጋር የተገናኙ አስተዳደራዊ ጥሰቶችን ወይም ብልሹ አሰራሮችን፣ የሥነ ምግባር ደንብ ጥሰቶች፣ የውጤት ተቀውሞዎችን እና ከምርጫ ጋር የተያያዙ የወንጀል ጥፋቶችን ሊያካትቱ ይችላሉ፡፡[123] በአጠቃላይ የተለያዩ የክርክር እና የቅሬታ አይነቶች በቅድመ ምርጫ፣ በምርጫ ቀን እና በድህረ ምርጫ የሚከሰቱ ተብለው ሊከፈሉ ይችላሉ፡፡

### 2.2.1. የቅድመ ምርጫ ክርክሮች

[123]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር፣ 57

በምርጫ አዋጅ ቁጥር 1162/2011 ላይ ከተመለከቱት የቅድመ ምርጫ ክርክሮች መካከል ከመራጮች ምዝገባ ጋር በተያዘ የሚነሱ ቅሬታዎች ፣ በእጩ ምዝገባ ወቅት የሚነሱ ቅሬታዎች ፣ ከፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎች እንዲሁም በህዝብ ሀብት ላይ አላግባብ መጠቀምን ፣ ስም ማጥፋትን ፣ አመጽ ማነሳሳትን እና የሥነ-ምግባር ደንቡን የሚጥሱ መግለጫዎች ማውጣትን ጨምሮ ህገወጥ የምርጫ ቅስቀሳ ማካሄድን የሚያካትቱ ናቸው፡፡[124]

### 2.2.2. የምርጫ ቀን ክርክሮች

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ላይ ከተመለከቱት የምርጫ ቀን ክርክሮች መካከል ሌላ ሰው መስሎ መቅረብን ፣ ከአንድ ጊዜ በላይ መምረጥን ፣ የድምፅ አሰጣጡን ሚስጥራዊነት አለማክበርንና በምርጫ ጣቢያዎች ውስጥ የሚደረግ ህገወጥ የምርጫ ቅስቀሳን ጨምሮ የድምጽ አሰጣጥ ሂደቱ ግድፈቶች ነበሩበት የሚሉ ቅሬታዎች ፣ የአንድን ሰው የመምረጥ መብት በሚነፍጉ ውሳኔዎች ላይ የሚቀርቡ ወይም የአንድን ሰው የመምረጥ መብት የሚቃወሙ አቤቱታዎች ፣ ጥቃትን ፣ ዛቻዎችን በተመለከተ የሚቀርቡ ቅሬታዎች ፣ በምርጫ ቀን የምርጫ ተግባራቶች ለመገናኛ ብዙሃን ፣ ለታዛቢዎች ወይም ወኪሎቻቸው ተደራሽ እንዳይሆኑ ተደርጓል የሚል ቅሬታ ፣ በፀጥታ አስከባሪዎች ጣልቃ ገብነት ነበር የሚሉ ቅሬታዎች ዋና ዋናዎቹ ናቸው፡፡[125]

[124]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር፣ 108፣አንቀጽ 152
[125]ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 50(2)፣54(1)፣121(8)፣130(4)፣143(11)፣157(2)(3)(ረ)፣154(1)(5)

### 2.2.3. የድህረ ምርጫ ቀን ክርክሮች

ከምርጫ ቀን በኋላ ከሚነሱ ክርክሮች መካከል ምርጫው የድምጽ ቆጠራ ግድፈቶች ነበሩበት የሚሉ ቅሬታዎች፣ የውጤት ማዳመርና ማስተላለፉ ሂደቱ ግድፈቶች ነበሩበት የሚሉ ቅሬታዎች እና የውጤት ይፋ አደራረግ ሂደቱ ግድፈቶች ነበሩበት የሚሉት ቅሬታዎች ይገኙበታል፡፡[126]

## 2.3. የምርጫ ክርክሮች ለመመልከት ስልጣን ያላቸው አካላት በኢትዮጵያ

በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 በኢትዮጵያ የምርጫ ክርክሮችን እንዲመለከቱ ስልጣን የተሰጣቸው አካላት የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ፣ በተለያዩ ደረጃዎች ያሉ የቅሬታ ሰሚዎች፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ መድረክ፣ የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ ምክር ቤት እና ስልጣን ያላቸው የፌደራል እና የክልል ፍርድ ቤቶች ናቸው፡፡[127]

### 2.3.1. የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች

የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በምርጫ ጣቢያ ፣ በምርጫ ክልል እና በክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የተቋቋሙ ሲሆኑ ሶስት አባላትን ይዘው ይዋቀራሉ፡፡

[126]ዝኒ ከማሁ፣አንቀጽ 58(6)፣60(1)፣62(2)፣131(2) እና 155
[127]ዝኒ ከማሁ

የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ከመራጮች ምዝገባ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች፣ የመምረጥ መብትን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች፣ ከድምፅ ቆጠራና ውጤቶች ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን የመመልከት የመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን አላቸው፡፡[128]

የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ከእጩ ምዝገባ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችንበመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን የመመልከት እንዲሁም ከመራጮች ምዝገባ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች፣ የመምረጥ መብትን ተግባራዊ ከማድረግ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች ከድምፅ ቆጠራና ውጤቶች ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን የምርጫ ጣቢያ ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣን አይተው የሚሰጡትን ውሳኔ በይግባኝ ይመለከታሉ፡፡[129]

የክልል ቅርንጫፍ ጽህፈት ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ደግሞ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ከእጩ ምዝገባ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎችን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ መሰረትየወሰነውን ውሳኔ በይግባኝ ይመለከታል፡፡[130]

### 2.3.2. የኢትዮጵያ ብሔራዊ ምርጫ ቦርድ

ከፖለቲካ ፓርቲ ምዝገባ ጋር የተያያዙ ቅሬታዎች፣ ማመልከቻ ሲቀርብለት የፓርቲን መተዳደሪያ ደንብ አፈፃፀም ጨምሮ የፖለቲካ ፓርቲ ውስጣዊ አለመግባባቶችን፣ የምርጫ ሥነ-ምግባር ደንብ መጣስ ወይም የሥነ-

[128]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር፣ 108
[129]ዝኒ ከማሁ
[130]ዝኒ ከማሁ

ምግባር ጥሰቶች ተከስተዋል በሚል የሚቀርቡ ቅሬታዎችን እንዲሁም የቆጠራና የውጤት ክርክሮች ላይ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሰጡት ውሳኔ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የማስተናገድ ስልጣን አለው፡፡[131]

### 2.3.3. ፍርድ ቤቶች

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከድምፅ ቆጠራና ውጤቶች ጋር ተያይዘው ለሚነሱ ቅሬታዎች ምርጫ ቦርድ በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎች የማስተናገድ ስልጣን ያለው ሲሆን የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ደግሞ ከእጩ ምዝገባ ጋር በተያያዘ የክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሚሰጡት ውሳኔዎች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የማስተናገድ ስልጣን ይሰጣቸዋል፡፡[132]

የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ደግሞ አንድ የፖለቲካ ፓርቲ ለመመዝገብ ብቁ መሆን አለመሆኑንየሥነ-ምግባር ጥሰቶችን እና የስነ ምግባር ደንቦችን መጣስ እንዲሁም የእጩ ምልክት አቤቱታዎችን በተመለከተ በሚነሱ ክርክሮች ላይ የምርጫ ቦርድ በሚሰጣቸው ውሳኔዎች ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን የማስተናገድ ስልጣን ይኖረዋል፡፡[133] እንዲሁም የምርጫ አዋጁ ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት፣ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተወሰኑ ስልጣኖችን ከመስጠት በተጨማሪ በአንቀጽ 152(8) እና 154(4) ስር ስልጣን ያላቸው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ

[131]ዝኒ ከማሁ
[132]ዝኒ ከማሁ
[133]ዝኒ ከማሁ

ቤቶች ከመራጮች ምዝገባና ከድምጽ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን እንደሚያስተናግዱ የሚገልጽ ቢሆንም ፍርድ ቤቶቹ የትኞች የክልል እና የትኞቹ የፌደራል ፍርድ ቤት እንደሆኑ የሚገልጸው ነገር የለም፡፡[134] በአጠቃላይ የኢትዮጵያ ምርጫና የፖለቲካ ፓርቲዎች አዋጅ ቁጥር 1162/2020 ከነችግሩም ቢሆን በኢትዮጵያ የምርጫ ክርክሮችን ለመፍታት ዝርዝር ማዕቀፎችን አስቀምጧል፡፡የኢትዮጵያ ምርጫ ቦርድን፣ የፌዴራልና የክልል ፍርድ ቤቶችን፣ የቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎችን እንዲሁም በስምምነት የምርጫ አለመግባባትን እንዲፈቱ ስልጣን የተሰጣቸው የፖለቲካ ፓርቲዎች የጋራ መድረክና ምክር ቤትን ጨምሮ የበርካታ አካላት ተሳትፎ ፣ አለመግባባቶች እንዲፈቱ እና የምርጫ ሒደቱ ታማኝነት እንዲረጋገጥ ይረዳል፡፡

## 3. የምርጫ ክርክርን በፍርድ ቤት ከመፍታት አንፃር በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ ማዕቀፍ ላይ ያሉ ሥነ-ስርዓታዊ ተግዳሮቶች

### 3.1. ልዩ የምርጫ ክርክሮችን ለመፍታት የሚያገለግል የሥነ-ስርዓት ህግ አለመኖር

በኢትዮጵያ የምርጫ ስርዓት ውስጥ የዳኝነት አካላት የምርጫ አቤቱታዎችና ቅሬታዎችን ተመልክተው ውሳኔ ለመስጠት ከሚያጋጥማቸው የተለመደ ችግር አንዱ የምርጫ ክርክሮችን ለመፍታት

[134] ዝኒ ከማሁ

የሚያገለግል ልዩ የሥነ-ስርዓት ህግ አለመኖር ነው።[135] የምርጫ ክርክሮች ባጠረ ጊዜ ውስጥ መፍትሄ የሚሹ በመሆናቸው በምርጫ ህጉ ውስጥ በተቀመጠው አጭር ጊዜ ውስጥ ጉዳዮችን በአግባቡ ለማስተናገድ የሚያስችልልዩ የሥነ-ስርዓት ህግ ያስፈልጋል፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ በኢትዮጵያ ውስጥ የሚነሱ የምርጫ ክርክሮችን ከሚመለከተው የምርጫ ቦርድ ወይም ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች ውሳኔ ተሰጥቶባቸው በይግባኝ መልክም ሆነ በቅሬታ መልክ ወደ ፍርድ ቤት ሲመጡ ጉዳዮቹን በሚታወቅ ፣ ግልጽና ፈጣን በሆነ መንገድ ለመዳኘት የሚያስችል ልዩ የምርጫ ሥነ-ስርዓት ሕግ አለመኖሩ በኢትዮጵያ ምርጫ ህግ ማዕቀፍ ላይ እንደ ችግር የሚነሳ ትልቅ ክፍተት ነው።[136] ይህም የምርጫ ክርክሮች የሚፈቱበትን ስርዓት ግልጽነትና ወጥነት የጎደለው እንዲሆን ስለሚያደርገው የምርጫ ሂደቱን እና ውጤቱን ህጋዊነት ሊያሳጣው ይችላል፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባላቸው መመዘኛዎች መሰረት የሚታወቅ እና ግልጽነት ያለው የምርጫ ክርክር

---

[135]ከምርጫ ክርክሮች ባህሪ አንጻር ከምርጫ ጋር ተያይዞ የሚነሱ ቅሬታዎችን የሚቀበልበትን፣ክርክሩን የሚመራበትን፣በክርክሩ ሂደት ተከራካሪዎች ስለሚኖራቸው ተነጻጻሪ የማስረዳት ግዴታ እና የማስረዳቱን ደረጃ እንዲሁም መሰል አግባብነት ያላቸው ዝርዝር ሂደቶችን በተወሰነ ጊዜና በአጭር ቀጠሮ እልባት ለመስጠት ይረዳ ዘንድ ልዩ የምርጫ ስነስርዓት ህግ እንደሚያስፈልግ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎት በመ/ቁ 230207 በሰጠው ውሳኔ ላይ አጽኖት መስጠቱን ልብ ይሏል፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከምርጫ ክርክሮች ልዩ ባህሪ አንጻር የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ከስድስተኛው አገራዊ ምርጫ ጀምሮ ተግባራዊ የሚደረግ የምርጫ ክርክሮችን ለመምራት የሚያገለግል ልዩ የምርጫ ስነሥርዓትና የማስረጃ ህግ ረቂቅ ለህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አቅርቦ ውድቅ መደረጉን ልብ ይበሉ፡፡

[136]ከዚህ ጋር በተገናኘ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ችሎቱ የኦነግ ፓርቲ አባላት የሆኑት እነ አራርሶ ቢቂላ ከምርጫ ቦርድ ጋር ያደረጉትን ክርክር በተመለከተ መዝገቡ ከምርጫ ቦርድ ተወስኖ ካበቃ በኋላ በክርክር ሂደት በተንዛዛ አካሄድ ሲመላለስ ቆይቶ ሰኔ 28 ቀን 2013 ዓ.ም ስድስተኛው ሃገር አቀፍ ምርጫ ከተጠናቀቀ በኋላ ክርክሩ እልባት ያገኘ መሆኑን መመልከት ይቻላል፡፡

የሚፈታበት ልዩ የሥነ-ስርዓት ሕግ ማዕቀፍ የምርጫውን ሂደት ትክክለኛነት ለማረጋገጥና የምርጫ ክርክሮችን ፍትሃዊ በሆነ መንገድ ለመፍታት አስፈላጊ እንደሆነ ለመረዳት ይቻላል፡፡[137] ለዚህም እንደ ምክንያት የሚነሳው እንዲህ ዓይነቱ ማዕቀፍ ቅሬታዎችን ለማቅረብ እና ለማስኬድ ግልጽ ሂደቶችን፣ የማስረጃዎችን አቀራረብና አመዛዘን እንዲሁም ውሳኔ አሰጣጡን በተመለከተ በግልጽ ማስቀመጥ በመቻሉ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ማዕቀፉ ሁሉም ወገኖች ከህጋዊ ሂደቱ እኩል ተጠቃሚ እንዲሆኑ፣ ክርክሮች በጊዜ፣ ፍትሃዊ እና ገለልተኛ በሆነ መንገድ እንዲፈቱ ያደርጋል፡፡ [138] ይህም የመወከልን፣ የመደመጥ መብትን ፣ ይግባኝ የመጠየቅ እና ምክንያታዊ ውሳኔ የማግኘት መብትን እንዲረጋገጥ ያደርጋል፡፡[139] ስለሆነም እንዲህ ዓይነት የሥነ-ስርዓት ሕግ ከሌለ የምርጫ ክርክሮች በዘፈቀደ አካሄድና ልዩነት ባለው መንገድ ሊዳኙ ይችላሉ፡፡ ይህም ለአድሏዊና ህገወጥ ተግባራት በር ሊከፍት ይችላል፡፡ይህ ደግሞ ህዝቡ በምርጫው ሂደት እና በውጤቱ ህጋዊነት ላይ ያለውን እምነት የበለጠ ሊሸረሽረው ይችላል፡፡ ስለሆነም ኢትዮጵያ በአለማቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ያላቸው መመዘኛዎችንና በአገራት ያለን ጥሩ ተሞክሮ ከግምት ያስገባ የምርጫ ክርክሮችን ለመፍታት የሚያስችል ልዩ የሥነ-ስርዓት ህግ ማዕቀፍ መዘርጋት አለባት፡፡ይህም የምርጫ ሒደቱ ፍትሐዊ ፣ ግልጽና

[137]Resolving Election Disputes in the OSCE Area: Towards a Standard Election Dispute Monitoring System, OSCE/ODIHR, Warsaw, 2000. See also Code of Good Practice in Electoral Matters (Venice Commission's Code of Good Practice), The Council of Europe, Venice, 2002 See also Inter-Parliamentary Union's Declaration on Criteria for Free and Fair Elections, 1994, Paragraph 4 (9).

[138]ዝኒ ከማሁ

[139]ዝኒ ከማሁ

ተአማኒ እንዲሆን ፣ ውጤቱም በሁሉም ፓርቲዎችና ባለድርሻ አካላት ተቀባይነት እንዲኖረው ይረዳል።

## 3.2. ጥቅልና ያልተለየ የዳኝነት ሥልጣን አቀማመጥ

የምርጫ አዋጁ 1162/2011 ለፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ፣ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትና ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የተወሰኑ ስልጣኖችን ለይቶ ከመስጠት በተጨማሪ በአንቀጽ 152(8) እና 154(4) ስር **ስልጣን ያላቸው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች** ከመራጮች ምዝገባና ከድምጽ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ያስተናግዳሉ በማለት የሚያስቀምጥ ቢሆንም ፍርድ ቤቶቹ የትኞች የክልል እና የትኞቹ የፌደራል ፍርድ ቤት እንደሆኑ የሚገልፀው ነገር የለም። ከዚህ በተጨማሪ ከእጩ ምዝገባ ጋር በተያያዘ የምርጫ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴ በሚሰጠው ውሳኔ ያልተስማማ አካል ወይም ቅሬታ ሰሚው ኮሚቴ ቅሬታው በቀረበለት በ7 ቀን ውስጥ ውሳኔ ካልሰጠው ይግባኙን ለክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት የማቅረብ መብት አለው በማለት አንቀጽ 153(8)ያስቀምጣል። ነገር ግን ቅሬታው የተፈጠረው በአዲስ አበባና ድሬደዋ ከሆነ ጉዳዩ ለየትኛው ፍርድ ቤት ይቀርባል የሚለውን ህጉ በግልጽ የሚለው ነገር የለም።

ከዚህ ጋር በተገናኘ በባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲና በምርጫ ቦርድ መካከል በተደረገው ክርክር ፓርቲው ለስድስተኛው አገር አቀፍ ምርጫ ለአዲስ አበባ የካ እና ንፋስ ስልክ ምርጫ ክልል እጩ አድርጎ

ያቀረባቸውን ግለሰቦች በወንጀል ተጠርጥረው በህግ ጥላ ስር የሚገኙ በመሆኑ በእጩነት ሊመዘገቡ አይገባም የሚል ውሳኔ በቅድሚያ በምርጫ ክልል አስፈፃሚ ኮሚቴው የተሰጠ ሲሆን ይህም ውሳኔ እስከ ምርጫ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት ድረስ ጸንቶ በይግባኝ ወደ ፍርድ ቤት ሲሄድ የቀረበው ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ነው፡፡[140] ይሄው ጉዳይ መሰረታዊ የህግ ስህተት አለበት ተብሎ ለሰበር ችሎቱ ሲቀርብለት የሰበር ችሎቱም በተቃራኒ ተከራካሪ አካል ወይም ተጠሪ በሆኑት የምርጫ ቦርድ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን ለማየት ስልጣን የለውም የሚለው ክርክር አለመነሳቱንና በኢፌዴሪ ህገ መንግስት አንቀጽ 80(2) መሰረት የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ውክልና የተሰጠው አቻ ተቋም መሆኑን በመግለጽ አዲስ አበባ እና ድሬደዋ ላይ ከእጩ ምዝገባ ጋር በተገናኘ ለሚነሱ የምርጫ ክልል ቅርንጫፍ ጽ/ቤት የመጨረሻ ውሳኔ የሚሰጥባቸው ጉዳዮችን በይግባኝ ተመልክቶ የመወሰን ስልጣን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት እንደሆነ ድምዳሜ ላይ ደርሷል፡፡ እዚህ ጋር ልብ ብለን መመልከት ያለብን ጉዳይ ምንድን ነው ህገ-መንግስታዊ ውክልናው ለክልል ፍርድ ቤቶች ደረጃው ተለይቶ ሲሰጥ አንዱ ምክንያት ተደራሽነትን ለማስፋት በሚል ከፌደራል ፍርድ ቤቶች ለክልል ፍርድ ቤቶች እንጂ በተገላቢጦሽ ሰበሩ እንደደረሰበት የተሳሳተ መደምደሚያ ከክልል ፍርድ ቤቶች ለፌደራል ፍርድ ቤቶች አቻነትን መሰረት ባደረገ መርህ

[140] Balderas vs NEBE, Federal Supreme Court Cassation Division, 2013, Case No 207000

አለመሆኑን ነው፡፡[141] ከዚህ በተጨማሪ የስረ ነገር ስልጣንን በሚመለከት ተከራካሪ ወገኖች ባያቀርቡም ክርክሩ የቀረበለት የበላይ ፍርድ ቤት ጉዳዩ ቀድሞ ቀርቦለት የተመለከተውና ውሳኔ የሰጠው የበታች ፍርድ ቤት ጉዳዩን የመመልከት ስልጣን የለውም ብሎ ካሰበ በራሱ ማንሳት እንደማይከለከል ከፍትሀ ብሔር ስነ ሥርዓት ህግ አንቀጽ 9(2) የምንረዳው ጉዳይ ነው፡፡ከዚህ በተጨማሪ በዋናነት እራሱ የሰበር ሰሚ ችሎቱ በክልልና በፌደራል ፍርድ ቤቶች መካከል የሚነሳን የስረ ነገር ስልጣን ጉዳይ በተመለከተ በየትኛውም ደረጃ ፍርድ ቤት ሲደርስ በተከራካሪዎች ባይነሳ እንኳን የስልጣን ጥያቄውን ፍርድ ቤቱ በራሱ አንስቶ ውድቅ ሊያደርግ እንደሚገባ በመዝገብ ቁጥር 151923ና 183483 ላይ አስገዳጅ የህግ ትርጉም ሰጥቶበታል፡፡[142] በጥቅሉ በምርጫ አዋጅ 1162/2011 ውስጥ ከእጩ ምዝገባ ጋር በተገናኘ ድሬዳዋና አዲስ አበባ ላይ ለሚነሳ ክርክር

[141]ከዚሁ ከምርጫ ጉዳይ ጋር በተያያዘ ቀድሞ ከደረሰበት መደምደሚያ ጋር በሚቃረን መልኩ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድቤት በመ/ቁ 193714 በሰጠው ውሳኔ ላይ ለክልሎች በህገመንግስቱ ተሰጥቷቸው የነበረው ውክልና በአዋጅ ቁጥር 322/1995 መሰረት ከተወሰኑት ላይ የተነሳ ስለሆነ የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ስልጣን የሆኑትን ጉዳዮች በውክልና የመዳኘት ስልጣን የለውም በማለት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ይህም በሌላ አነጋገር በክልል ጠቅላይ ፍርድቤቶች እንዲታይ በህጉ አንቀጽ 152(8) ላይ የተመለከቱትን ጉዳዮች የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት ህገመንግስታዊው ክልናውን መሰረት በማድረግ መመልከት አይችልም ወደሚል መደምደሚያ ያመጣል፡፡ ምክንያቱም የተሰጠው ውክልና ከተነሳ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድቤት የማየት ስልጣኑ ወደኂላ ስለማይመለስ ማለት ነው፡፡ ስለሆነም ይህ በጥቅሉ የሚያሳየን የህጉን ጉልህ ክፍተት ሲሆን ይህ ክፍተትም በተግባር ፍርድቤቶቻችንን እየፈተነና የበለጠ ጉዳዮችን ወደማወሳሰብና ኢ-ተገማች ወደመሆን እየወሰዳቸው መሆኑን ነው፡፡

[142]እዚህ ጋር አብሮ መታየት ያለበት ጉዳይ የ/ፍ/ስ/ስ/ህ/ቁ9(2) የሚያገለግለው ጉዳዩን በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ለሚያይ ፍርድቤት ነው የሚል ክርክር ከህጉ አንጽር ቢነሳ ሚዛናዊ ቢሆንም ነገር ግን የስረነገር ስልጣን ጉዳይ ከሆነ በየትኛውም የፍርድቤት እርከን ላይ በባለጉዳዮቹ ባይነሳ እንኳን ፍርድቤቱ በራሱ አነሳሽነት አንስቶ ውድቅ ማድረግ ያለበት ስለመሆኑ በተጠቀሱት መዝገብ ቁጥሮች የተሰጠው የህግ ትርጉም በየትኛውም እርከን በሚገኙ ፍርድቤቶች ላይ አስገዳጅ ውጤት ያለው ስለመሆኑ ልብ ይሏል፡፡

እንዲሁም ከመራጮች ምዝገባና ከድምጽ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ለመፍታት ኃላፊነት የተሰጠው ፍርድ ቤት ግልጽ በሆነ መንገድ ይህ ነው ተብሎ አለመቀመጡ በምርጫ ወቅት ክርክሮች ሲከሰቱ ውዥንብርን ሊያስከትል እንዲሁም የምርጫ ክርክር አፈታት ሂደቱን ነፃነት እና ገለልተኝነት ሊያሳጣው ይችላል።ይህ ደግሞ በምርጫ ሂደቱ ላይ የህዝብ አመኔታ ማጣትና በምርጫ ክርክሮች አያያዝ ላይ ያለውን አድሎአዊ ግንዛቤን ሊያስከትል ይችላል። በተጨማሪም ፣ በዓለም አቀፍ ደረጃ ተቀባይነት ባላቸው መመዘኛዎች መስፈርቶች መሰረት የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ለሁሉም እጩዎች እና የፖለቲካ ፓርቲዎች ተደራሽ መሆን አለባቸው።የምርጫ ክርክሮችን ስለሚመለከተው ፍርድ ቤት ግልጽ ሥነ-ስርዓትና መመሪያ ከሌለ ከመንግስት በተቃራኒ የሚሰለፉ የፖለቲካ ፓርቲዎች የክርክር አፈታት ሂደቱን ለመጠቀም ከፍተኛ ፈተናዎች ሊገጥሟቸው ይችላሉ።

### 3.3. በፍርድ ቤቶች የሚሰጡ ውሰኔዎች የመጨረሻ መሆኑ አለመገለፁ

የኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ 1162/2011 ፍርድ ቤቶች በይግባኝ ሰሚ ደረጃ አይተው የሚሰጧቸውን ውሳኔዎች በተመለከተ የመጨረሻ ስለመሆናቸው የሚገልፀው ነገር የለም።በአለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ጥሩ ተሞክሮዎች የምርጫ ህጎች ከምርጫ ሂደት ጋር የተያያዙ ክርክሮችን ለመፍታት ውጤታማ፣ ገለልተኛ እና ግልፅ ስልቶችን ማስቀመጥ እንደሚገባ

ይገልፃሉ፡፡[143] ከዚህ ውስጥ አንዱ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ውሳኔ የመጨረሻ አድርጎ መቀበልን ይጠይቃል፡፡[144] ከዚህ ጋር በተያያዘ በይግባኝ ሰሚ ችሎት የሚሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻ ስለመሆናቸው በኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ ላይ በግልጽ አለመቀመጡ የምርጫውን ሂደት ተአማኒነት እና ህጋዊነት ላይ ጥያቄ ሊያስነሳ ይችላል፡፡እንዲሁም ውዥንብር እንዲፈጠር እና ክርክሮች እንደገና እንዲያገረሹ ሊያደርግ ይችላል፡፡ በዚህም የክርክር አፈታት ሂደቱን በማራዘም የምርጫውን ውጤት ይፋ ለማድረግ ያስቸግራል፡፡

ከዚህ ጋር በተያያዘ በባልደራስ ለእውነተኛ ዴሞክራሲ ፓርቲና በምርጫ ቦርድ መካከል በተደረገው ክርክር ፓርቲው እጩ አድርጎ ያቀረባቸው እስክንድር ነጋ ፣ ሞገስ ቸኮልና ቀለብ ስዩም በወንጀል ተጠርጥረው በህግ ጥላ ስር የሚገኙ በመሆኑ በእጩነት ሊመዘገቡ አይገባም የሚል ውሳኔ በምርጫ ክልል አስፈፃሚ ኮሚቴው ተሰጥቶ እስከ ፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ድረስ ጸንቷል፡፡[145] ነገር ግን ጉዳዩ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈጽሞበታል ተብሎ በአመልካች ለሰበር ሰሚ ችሎቱ ሲቀርብ ተጠሪ የሆነው ምርጫ ቦርድ ከክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በላይ ጉዳዩን ሊመለከት የሚችል ፍርድ ቤት ስለመኖሩና ስልጣን ያለው ስለመሆኑ በህጉ አንቀጽ

[143]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 43፣ገጽ 206 see also Code of Good Practice in Electoral Matters (Venice Commission's Code of Good Practice), The Council of Europe, Venice, 2002.

[144]Guidelines for Understanding, Adjudicating, and Resolving Disputes in Elections, International Foundation for Electoral Systems, Washington DC, 2011, pp.96 See also Code of Good Practice in Electoral Matters (Venice Commission's Code of Good Practice), The Council of Europe, Venice, 2002

[145]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 140

153(8) ላይ የተመለከተ ነገር ስለሌለ ውሳኔው የመጨረሻ ነው፡፡ ስለዚህም ሰበር ሰሚ ችሎቱ ጉዳዩን የመመልከት ስልጣን የለውም በማለት የተከራከሩ ሲሆን የሰበር ችሎቱም በተቃራኒ ሌላ የይግባኝ እርከን ስለመኖሩ በህጉ ያልተመለከተ በመሆኑ በጉደዩ ላይ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤቱ የሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ ነው ተብሎ ይወሰዳል በሚል መላምት ጉዳዩ ለሰበር መቅረብ እንደሚችል መደምደሚያ ላይ ደርሷል፡፡ ስለሆነም እዚህ ጋር መመልከት ያለብን ነገር ምንድነው ከእጩ ምዝገባ ጋር በተያያዘ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት በይግባኝ የቀረበለትን ጉዳይ ተመልክቶ የሚሰጠው ውሳኔ የመጨረሻ መሆኑ በህጉ ላይ ተመላክቶ ቢሆን ኖሮ እንዲህ አይነት መፍትሄ አልባ የክርክር አውድ የማይፈጠር መሆኑን ነው፡፡ እንዲሁም በተጨማሪ መታየት ያለበት ጉዳይ በኢትዮጵያ የህግ ስርዓት ውስጥ መሰረታዊ የህግ ስህተት ተፈፅሞብኛል የሚል ተከራካሪ ወገን ክርክሩን ለሰበር ሰሚ ችሎቱ የማቅረብ መብት አለው፡፡ እንዲህ ደግሞ ከሆነ ተከራካሪው በስር ፍርድ ቤቶች የመጨረሻ ውሳኔ ከተሰጠበት ቀን ጀምሮ የሚታሰብ ቅሬታውን ለሰበር ሰሚ ችሎቱ የማቅረቢያ 90 ቀን ጊዜን ይጎናፀፋል፡፡[146] ይህ ከሆነ ደግሞ የምርጫ ክርክሮችን እልባት ለመስጠት ከሚያስፈልጋቸው አጭር ጊዜ አንፃር አብሮ የሚሔድ አይደለም፡፡[147] ስለሆነም የምርጫ አዋጁ በይግባኝ ሰሚ ችሎቶች የሚሰጡ ውሳኔዎች የቱ ጋር የመጨረሻ እንደሚሆኑና በሰበር መታየትም

[146] Ethiopia federal court establishment proclamation,1234/2015, art 27(3)

[147]ከምርጫ ክርክሮች ባህሪ አንጻር ለክርክሮች በተወሰነ ጊዜና በአጭር ቀጠሮ እልባት ለመስጠት ይረዳ ዘንድ ልዩ የምርጫ ስነስርዓት ህግ እንደሚያስፈልግ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚችሎት በመ/ቁ 230207 በሰጠው የህግትርጉም ላይ አጽኖት ሰጥቷል፡፡

ካለባቸው በአዋጅ ደረጃ የተፈቀደውን 90 ቀን ከምርጫ ልዩ ባህሪ አንፃር አሳጥሮ የሚደነግግ ማዕቀፍ በምርጫ ህጉ ውስጥ መቀመጥ ነበረበት፡፡ ምክንያቱም የምርጫ ጉዳዮች ለሰበር ይቀርባሉ አይቀርቡም እንዲሁም በምን ያህል ጊዜ ይቀርባሉ የሚሉትን ጉዳዮች በደንብ ወይም በመመሪያ ይመለስ/ይደንገግ ቢባል በአዋጅ ደረጃ የተሰጡ መብቶችን በደንብ ወይም በመመሪያ መሻር ነው የሚሆነው፡፡ ይህ አይነቱ ተግባር ደግሞ ከመሰረታዊ የህግ ተዋረድ ፅንሰ-ሀሳብ ጋር ይጋጫል፡፡ ከምርጫ ሂደት ጋር በተያያዘ የሚነሱ ክርክሮች ላይ ይግባኝ ሰሚው ፍርድ ቤት የሚሰጠውን ውሳኔ የመጨረሻ ስለመሆኑ በግልፅ ማስቀመጥ እንደሚገባ አሁን ላይ ያሉ አለም አቀፍ ጥሩ ተሞክሮዎች ያሳያሉ፡፡ይህም የሚያካትተው ይግባኝ የሚጠየቅበትን ጊዜ ፣ ይግባኝ የማቅረብ ሂደቶችንና ውሳኔዎች የመጨረሻ እና አስገዳጅ የሚሆኑበትን ደረጃ መግለፅን ይጨምራል፡፡[148] ለማጠቃለል ያህል በኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ 1162/2011 ይግባኝ ሰሚ ችሎቶች የሚሰጧቸው ውሳኔዎች የመጨረሻ መሆን አለመሆንላይ ግልፅ ድንጋጌ አለመኖሩ ከአለም አቀፍተሞክሮ አንፃር እንዲሁም በተግባርም ፍርድ ቤቶቻችን ላይ እየፈጠረ ካለው ውዝግብ አንጻር በምርጫ ህጉ ላይ ያለ እንደ ትልቅ ችግር ተደርጎ የሚነሳ ነው፡፡የምርጫ ሕጎች እና ስርዓቶች የክርክር አፈታት ሂደትን ግልፅነት ፣ ፍትሃዊነት እና ተአማኒነት ለማረጋገጥ እንዲሁም ሂደቱን ካልተፈለገ እርዝማኔና ንትርክ ለመከላከል ሲባል በይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤት የሚሰጡት ውሳኔዎች የመጨረሻ ስለመሆናቸው በግልፅ ማሰቀመጥ ያስፈልጋል፡፡

[148]የግርጌ ማስታወሻ ቁጥር 144

### 3.4. ጠቅላላ ይርጋና ከአቅም በላይ የሆነ ችግር ከግምት አለማስገባት

በኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ 1162/2011 አንቀፅ 151(13) እንደተገለፀው ከመራጮች ምዝገባ ፣ ከእጩ ምዝገባ ፣ ከድምፅ አሰጣጥ እና በድምጽ ቆጠራና ውጤት ጋር በተያያዘ በአዋጁ አንቀፅ 152-155 ስር የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች ካለፉ አቤቱታ የማቅረብ መብቱ በይርጋ እንደሚታገድ ይገልፃል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ለምሳሌ በህጉ የተቀመጠው የምዝገባ ጊዜ ካለፈ በኋላ አንድ መራጭ ሙሉ በሙሉ መመዝገብ እንዳይችል የሚከለክል ድንጋጌ ሲሆን ይህም ተቀባይነት ካላቸው አለማቀፍተሞክሮዎች አንጻር ሲታይ እንደ ትልቅ ተግዳሮት ተደርጎ የሚወሰድ ነው፡፡[149] ምክንያቱም እንዲህ አይነቱ የክልከላ ተግባር ከአቅም በላይ በሆነ ክስተት ምክንያት ሳይመዘገቡ የቀሩ መራጮችንም የሚከለክል በመሆኑ ነው፡፡ በአለም አቀፍ መመዘኛዎች መስፈርት መሰረት ሁሉም ብቁ መራጮች በምርጫ ሂደት ውስጥ የመሳተፍ እድል እንዲኖራቸው ማድረግን ታሳቢ ያደረጉየምርጫ ህጎች እና ሂደቶች እንዲነደፉ ይጠይቃሉ፡፡ይህም የመራጮች ምዝገባ አሰራር ተደራሽ ፣ ግልፅ እና ሁሉንም ያካተተ መሆኑን ማረጋገጥ እና ብቁ የሆኑ መራጮች

[149] The Carter Center, Election Obligations and Standards Database, <https://eos.cartercenter.org>, accessed 25 June 2023 see also Guidelines for Understanding, Adjudicating, and Resolving Disputes in Elections, Interna-tional Foundation for Electoral Systems, Washington DC, 2011. Pp.82 See also Code of Good Practice in Electoral Matters (Venice Commission's Code of Good Practice), The Council of Europe, Venice, 2002

እንዳይመዘገቡ ያደረጉ ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶችን ከግምት ውስጥ ያስገባ መሆኑን ማረጋገጥን ይጨምራል፡፡

በኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ ውስጥ የምዝገባ ጊዜ ካለፈ በኋላ በማንኛውም ሁኔታ መራጮች እንዳይመዘገቡ የሚከለክለው ድንጋጌ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት መመዝገብ ያልቻሉትንም የመምረጥ መብታቸውን እንዳይጠቀሙ ያደርጋል፡፡በአለም አቀፍ ደረጃ ባሉ ጥሩ ተሞክሮዎች መመዘኛ መስፈርት መሰረት የመራጮች ምዝገባ ቀነ-ገደብ ሙሉ በሙሉ ዝግ መሆን እንዳሌለበት እና ከቁጥጥር ውጪ በሆኑ ሁኔታዎች እንደ የተፈጥሮ አደጋዎች ፣ ግጭቶች እና ሌሎች የአቅም ማነስ ክስተቶች ምክንያት የመመዝገቢያ ጊዜ ያለፈባቸውን መራጮች ሁኔታን ከግምት ያስገባ አማራጭ መኖር እንዳለበት ይገለፃል፡፡[150] ይህ ሁሉም ብቁ መራጮች በምርጫው ሂደት ውስጥ ፍትሃዊ በሆነ መንገድ የመሳተፍ እድል እንደሚኖራቸው ያረጋግጣል፡፡

## 3.5. ከመራጮች ምዝገባ ጋር የተያዙ ተግዳሮቶች

በዓለም አቀፍ ደረጃ ያሉ ጥሩ ተሞክሮዎች እንደሚጠቁሙት ከሆነ የምርጫ እና ልዩ የምርጫ ሥነ-ስርዓት ህግ ከእጩ ምዝገባ ጋር በተያያዘ

[150] ዝኒ ከማሁ

ለሚነሱ ክርክሮች መፍትሄ የሚሰጥበትን ሂደት በግልፅ ማስቀመጥ አለባቸው።[151]ይህም ክርክሮችን ለመፍታት ኃላፊነት ያለበትን ፍርድ ቤት የመለየት ፣ ክርክሮችን ወደ ፍርድ ቤት ሲቀርቡ የሚፈቱበት ግልፅ ጊዜ ፣ ቅሬታ የማቅረብ እና የማስተናገድ ሂደቶችን ማካተትን ይጠይቃል። ከዚህ ጋር በተያያዘ በኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ 1162/2011 አንቀፅ 152(8) ላይ ከመራጮች ምዝገባ ጋር በተገናኘ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን በጥቅሉ ስልጣን ያላቸው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች ያስተናግዳሉ በማለት የሚያስቀምጥ ቢሆንም ፍርድ ቤቶቹ የትኞች የክልል እና የትኞቹ የፌደራል ፍርድ ቤት እንደሆኑ የሚገልፀው ዝርዝር ነገር የለም። እንዲሁም ከመራጮች ምዝገባ ጋር በተያያዘ የሚነሱ አለመግባባቶችን ለመዳኘት የሚቀርብለት ስልጣን ያለው ፍርድ ቤት በምን ያህል ጊዜ ውስጥ ክርክሩን ሰምቶ ውሳኔ ይሰጣል የሚለው የጊዜ ገደብ በአንቀፁ ላይ አልተቀመጠም። ከዚህ በተጨማሪ ስልጣን ያላቸው ፍርድ ቤቶች የሚባሉት ጉዳዩን የሚያዩት በይግባኝ ነው ወይስ በመጀመሪያ ደረጃ የሚለውን በግልፅ አያመለክትም።እንዲሁም በግልፅ አለመቀመጡ በራሱ ይዟቸውየሚመጣው ችግሮች አሉ። ለምሳሌ ጉዳዩ የሚታየው በይግባኝ ደረጃ ከሆነ ውሳኔው የመጨረሻ ስለመሆኑ መገለፅ አለበት ካልሆነ ክርክሩ ማብቂያ የሌለው እንዲሆን በር ይከፍታል። በተጨማሪ በፍርድ ቤት የሚታየው በመጀመሪያ ደረጃ ከሆነ የይግባኝ

[151] Handbook for Monitoring Administrative Justice, OSCE/ODIHR and Folke Bernadotte Academy, Warsaw, 2013, <https://www.osce.org/office-for-democratic-institu-tions-and-human-rights/105271>.

መብት እንዲጠበቅለት የሚያደርግ ቢሆንም የስርዓት መፋለስ እንዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## 3.6. ከሥነ-ምግባር ጥሰቶች ጋር የተያዙ ተግዳሮቶች

ማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ ወይም በድርጊቱ ቀጥተኛ ተጎጂ የሆነ ሰው ወይንም በጉዳዩ ላይ መብት ወይም ጥቅም ያለው አካል በማንኛውም የፖለቲካ ፓርቲ ፣ የግል እጩ ተወዳዳሪ ፣ የፖለቲካ ፓርቲ መሪ ፣ አባል ፣ ወኪል ወይም ተጠሪ የህግ ጥሰት ተፈፅሟል ብሎ ካሰበ ቅሬታ የማቅረብ መብት እንዳላቸው በህጎቹ የተቀመጠ ሲሆን የሚፈፀሙ የሥነ-ምግባር ጥሰቶች ተከስተዋል ተብለው ቀርበው የብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ዋና ጽ/ቤት በሚሰጠው ውሳኔ ላይ የሚቀርቡ ቅሬታዎችን የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የማስተናገድ ስልጣን እንዳለው የምርጫ አዋጅ 1162/2011 አንቀፅ 149 ላይ ተመላክተዋል፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የአዋጁን አንቀፅ 148 ፣ 149 እና 150 በአፅንኦት ስንመለከት የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የሥነ-ምግባር ጥሰቶችን በተመለከተ በቅድሚያ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ የማየት እንዲሁም በመቀጠል ጉዳዩን በይግባኝ ስልጣኑ መመልከት እንደሚችል ያመለክታል፡፡ ይህ ማለትም የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ቢቀርብለት ኖሮ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ሊመለከተው ይችል የነበረውን አንድን ጉዳይ ቦርዱ ተመልክቶ ውሳኔ ሲሰጥበት መልሶ በይግባኝ ይመለከተዋል ማለት ነው፡፡ ይህም አንድ ፍርድ ቤት እራሱ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ ሊያየው የሚችለው ጉዳይን መልሶ በይግባኝ የማየት ስልጣንን ያጎናፅፋል፡፡ ይህም

መሰረታዊ ከሆነው የይግባኝ ፅንሰ ሃሳብና ይግባኝ ያስፈለገበት ምክንያት አንፃር ውጤት አልባ የሆነ ድንጋጌ ነው፡፡ እንዲሁም ከዚህ በተጨማሪ በክልል ደረጃ የክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤቶች ህገ መንግስታዊ ውክልና ስልጣናቸውን ተጠቅመው ጉዳዩን ማየት ስለመቻል አለመቻላቸው የሚገልፀው ነገር የለም፡፡ ከዚህ ጋር በተገናኘ በአመልካች የአርጎባ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅትናበተጠሪ ሙሳ ያሲን[152] መካከል በተደረገው ክርክር አመልካች የተጠሪ አቤቱታ በመጀመሪያ በፓርቲዉ ዉስጥ በየደረጃዉ ላሉ አካላት ቀጥሎም ለምርጫ ቦርድ ቀርቦ ሳይወሰን በቀጥታ ክስ መልክ ለፍርድ ቤት ቀርቦ መታየቱ መሰረታዊ የሕግ ስህተት ነው በማለት ያቀረበ ሲሆን ተጠሪም በበኩሉ ፍርድ ቤቱ በአንቀጽ 150 ላይ በተደነገገዉ መሰረት በቀጥታ ክሱ ቀርቦለትም ሆነ ቦርዱ በሰጠዉ ዉሳኔ ላይ

[152] Argobal democratic party vs Musa Yasin, Federal Supreme Court Cassation Division, 2013, Case No 193714 በአመልካች በአርጎባ ሕዝብ ዲሞክራሲያዊ ድርጅትና በተጠሪ ሙሳ ያሲን ቡሎ መካከል በተደረገ ክርክር የሰበር ተጠሪ ለአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት የፖለቲካ ድርጅት ሊቀመንበር ሆነዉ እያገለገሉ እያለ የድርጅቱ ሥራአስፈጻሚዎች በቀን 22/02/2012 ዓ/ም አካሄድን ባሉት ስብሰባ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ 23/1 መሰረት የድርጅቱን ሊቀመንበር ገምግሞ የማገድ ሥልጣን የማዕከላዊ ኮሚቴ ሆኖ እያለ ከሥልጣናቸዉ ዉጭ ከኃላፊነት ሥላገዱኝ እገዳዉ የመተዳደሪያ ደንቡን አንቀጽ 16/5ን በሚቃረን አኳኋን ጭምር የተፈጸመ ስለሆነ የሥራአስፈጻሚዉ ኮሚቴ ያስተላለፈብኝ እገዳ እንዲነሳልኝይ ወሰንልኝ በማለት ጥያቄ ያቀረቡ ሲሆን የሰበር አመልካች በበኩላቸው ፍርድቤቱ ተጠሪ በቀጥታ ያቀረቡትን ክስ ተቀብሎ የመዳኘት ሥልጣን የለዉም የሚል መቃወሚያ በማስቀደም ተጠሪ ከድርጅቱ ሊቀመንበርነት እንዲታገዱ የተወሰነዉ በድርጅቱ መተዳደሪያ ደንብ መሰረት በሥራ አሥፈጻሚ ኮሚቴ አቅራቢነት በድርጅቱ ማእከላዊ ኮሚቴ በተሰጠ ዉሳኔ ስለሆነ እግዱ ሊጸድቅ ይገባል በማለት ነው፡፡ ክርክሩን በመጀመሪያ ደረጃ ሥልጣን ያየዉ የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድቤት በመ/ቁጥር 4749 ላይ በቀን 28/07/2012 ዓ/ም በሰጠዉ ብይን ፍርድቤቱ ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን እንዳለዉ በመግለጽ የአመልካችን ተቃዉሞ ዉድቅ አድረጓል፡፡ ፍሬ ነገሩን በተመለከተም የድርጅቱ ሥራአስፈጻሚ ኮሚቴ ተጠሪን ያገደበትን ዉሳኔ ለማእከላዊ ኮሚቴ አቅርቦ ቢያ ስጸድቅም ሥራአስፈጻሚ ኮሚቴዉ ተጠሪን ከሊቀመንበርነት ያገደዉ በሌለዉና ባልተሰጠዉ ሥልጣን ነዉ በማለት እግዱ የሕግ አግባብነት የለዉም በማለት ሽሮ ወስኗል፡፡

የቀረበለትን አቤቱታ በመመልከት ተገቢዉን ዉሳኔ ለመስጠት ስልጣን ያለዉ በመሆኑ የተፈጸመ የሕግ ስህተት የለም በማለት ተከራክሯል፡፡

የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሰበር ሰሚ ችሎትም መዝገቡን ከመረመረ በኋላ አንቀጽ 149 እና 150 ድንጋጌዎች የሚገኙት የምርጫ ሥነ ምግባርን በሚመለከተዉ ክፍል ስድስት ዉስጥ ባለዉ የሥነ ምግባር ጥሰቶችና ስለሚወሰዱ እርምጃዎች በሚደነግገዉ ሦስተኛ ምእራፍ ስር እንደመሆናቸዉ አፈጻጸማቸዉ ከክፍሉ አንጻር ሊሆን እንደሚገባ እንዲሁም በአንቀጽ 149 መሰረት የሥነ ምግባር ጥሰቶችን በተመለከተ ቦርዱ በሚሰጠዉ አስተዳደራዊ ዉሳኔ ቅሬታ ያለዉ ወገን አቤቱታዉን ሲያቀርብ ቅሬታዉ እየቀረበ ያለዉ አስቀድሞ በቦርዱ በተሰጠ ዉሳኔ ላይ በመሆኑ በድንጋጌዉ መንፈስ መሰረት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት የቦርዱን ዉሳኔ እንደገና በዳኝነት የመመርመር ሥልጣን አለዉ፡፡ በተጨማሪም በአንቀጽ 150 ሥር የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀጥታ ክስ ጉዳዩ ቀርቦለት የመዳኘት ሥልጣን የሚኖረዉ በማናቸዉም ከፖለቲካ ፓርቲ ጋር በተያያዙ ጉዳዮች ላይ ሳይሆን ይህ ድንጋጌ የሚገኝበት የሕጉ ክፍል ስድስት ከሚመለከተዉ የምርጫ ሥነ ምግባር ጋር በተያያዘ ቦርዱ ዉሳኔ በማይሰጥባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሆኑን የክፍሉ አጠቃላይ ይዘት እና የዚሁ ድንጋጌ ይዘትና መንፈስ ያስገነዝባል በማለት ውሳኔ ሰጥቷል፡፡ በተጨማሪም እንዲህ አይነት አለመግባባትን በሚመለከት ዳኝነት ተጠይቆበት ቀጥታ ክስ ለክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ሲቀርብ በአዋጅ ቁጥር 1133/2011ም ሆነ በአዋጅ ቁጥር 1162/2011 ክሱን ተቀብለው እንዲዳኙ ሥልጣን አልተሰጣቸውም፡፡ እንዲሁም ይህ ጉዳይ ለአፋር ክልል ጠቅላይ

ፍርድ ቤት በይግባኝ መልክ አልቀረበለትም እንጂ ቢቀርብለት እንኳን የአፋር ክልል ጠቅላይ ፍርድ ቤት የፌዴራል ከፍተኛ ፍርድ ቤትን ሥልጣን በዉክልና እንዲዳኝ በሕገ መንግስቱ የተሰጠዉ ሥልጣን በአዋጅ ቁጥር 322/1995 ስለተነሳ የክልሉ ጠቅላይ ፍርድ ቤት በአዋጅ ቁጥር 1133/2011 አንቀጽ 17(1) መሰረት ጉዳዩን የመዳኘት ሥልጣን የለዉም በማለት ውሳኔ የሰጠ ሲሆን ከዚህ አንጻር መታየት ያለበት ዋናው ጉዳይ ሁለቱ አንቀጾች ግልጽ ካለመሆናቸው የተነሳ በተለያየ ደረጃ ያሉ ፍርድ ቤቶች ሊታረቅ የማይችል የተለያየ አይነት አተረጓጎምን እንዲከተሉ እንዳደረጋቸው ለመረዳት ይቻላል፡፡

ከዚህ በተጨማሪ የፌደራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት ይዘትና መንፈሱን ጠቅሶ የተረጎመበት አካሄድ ጥሩ ሆኖ ሳለ የደረሰበት መደምደሚያ ግን አሁንም ቢሆን በአንቀጹ ላይ ያለውን ብዥታ የሚያጠራ ሆኖ አልተገኘም፡፡ ምክንያቱም የሰበር ችሎቱ በአንቀጽ 150 ላይ የተመለከተው አንቀጽ 148ን የሚጠቅሰው ሁለተኛ ሃሳብ ተፈጻሚነት ድንጋጌው የሚገኝበት የሕጉ ክፍል ስድስት ከሚመለከተዉ የምርጫ ሥነ ምግባር ጋር በተያያዘ ቦርዱ ዉሳኔ በማይሰጥባቸዉ ጉዳዮች ላይ መሆኑን የሚገልጽ ቢሆንም የአንቀጽ 148 መግቢያ በበኩሉ ቦርዱ እንደየተፈጠረው የጥፋት ሁኔታ በመመልከት ለዐቃቢ ህግ ሊመራ የሚችል መሆኑ እንደተጠበቀ ሆኖ የተጠቀሱትን የቅጣት አይነቶች በህጉ ክፍል ስድስት ለተመለከቱት ሁሉም የዲስፕሊን ግድፈቶች ሊቀጣ እንደሚችል የሚገልጽ ሆኖ አንገኘዋለን፡፡ ከዚህ በተጨማሪ ከምርጫ ሥነ ምግባር ጋር በተያያዘ የሚነሱ ቅሬታዎች የወንጀል ተጠያቂነት ሊፈጥሩ መቻላቸው እንደተጠበቀ ሆኖ በመሰረታዊነት

ተፈጥሯዊ ባህሪያቸው አስተዳደራዊ እንደመሆኑ መጠን በቀጥታ ለፍርድ ቤት ሊቀርቡ ይችላሉ ወደሚል መደምደሚያ ለመድረስ የሚያስደፍር አይደለም፡፡ ነገር ግን ከዚህ በተቃራኒ ሰበር ሰሚ ችሎቱ የሕጉ ክፍል ስድስት ከሚመለከተዉ የምርጫ ሥነ ምግባር ጋር በተያያዘ ቦርዱ ዉሳኔ በማይሰጥባቸዉ ጉዳዮች ክሱ ለፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቀጥታ ይቀርባል ሲል የደረሰበት መደምደሚያ ፍጹም ስህተት ነው፡፡

## 3.7. የዕጩዎች የምርጫ መለያ ምልክት ጋር የተያዙ ተግዳሮቶች

ማንኛውም የግል እጩ ተወዳዳሪ ወይም የፖለቲካ ፓርቲ ከእጩ የምርጫ መለያ ምልክት ጋር በተያያዘ ቅሬታ የማቅረብ መብት እንዳላቸው በህጎቹ የተገለፀ ሲሆን ቅሬታው የሚቀርብበትን ሁኔታ በተመለከተ ለፖለቲካ ፓርቲዎች የፖለቲካ ፓርቲዎችን የመለያ ምልክት በተመለከተ በመጀመሪያ ደረጃ ቅሬታው የሚቀርበው ለብሄራዊ የምርጫ ቦርድ ስራ አመራር ቦርድ ሲሆን ለግል እጩዎች ደግሞ አማራጭ ባለው መልኩ ለብሄራዊ ምርጫ ቦርድ ክልል ቅርንጫፍ ፅ/ቤት ወይም ለዋናው መስሪያ ቤት ማቅረብ እንደሚችሉ ህጎቹ ይገልፃሉ፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ የኢትዮጵያ ምርጫ አዋጁ 1162/2011 ከእጩ የምርጫ መለያ ምልክት ጋር በተያያዘ የሚፈጠሩ ክርክሮች በምን አግባብ ወደ ፍርድ ቤት መጥተው ይፈታሉ የሚለውን ጉዳይ በተመለከተ የሚገልፀው ነገር የለም፡፡ ሆኖም ግን የምርጫ ቦርድ ማቋቋሚያ አዋጅ 1133/2011 አንቀፅ 17(1) የምርጫ አዋጁን አንቀፅ 16 መሰረት አድርጎ ወጥቶ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት ጉዳዩን በይግባኝ ማየት እንደሚችል ይገልፃል፡፡ ከዚህ አንፃር የምርጫ

አዋጁ እንዲህ ያሉ ጉዳዮችን በግልፅ ማስቀመጥ ሲገባው አለመግለፁ እንደ ትልቅ ችግር የሚወሰድ ነው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ 1133/2011 አንቀፅ 17 በራሱ ውሳኔው የሚሰጥበት ጊዜንና በይግባኝ ደረጃ የሚታይ ስለመሆኑ ቢገልፅም የውሳኔው መጨረሻ መሆን አለመሆንን እንዲሁም የሚቀርቡት ክርክሮች የሚፈቱበት ልዩ ሥነ-ስርዓት መኖር አለመኖሩን በተመለከተ ግን የሚገልፀው ነገር የለም፡፡

# 4. ማጠቃለያና የመፍትሄ ሃሳቦች

## 4.1. ማጠቃለያ

የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት በምርጫ ሂደት ውስጥ ሊፈጠሩ የሚችሉ ክርክሮችን ለመፍታት የተቀመጡ ስልቶችን እና ሂደቶችን በመጠቀም ከምርጫ በፊት ፣ በምርጫ ወቅት እና ከምርጫ በኋላ ለሚፈጠሩ አግባብ ያልሆኑ ድርጊቶች ወይም አሰራር በህጋዊ መንገድ የሚቃወሙበት ስርዓት ነው፡፡ ምርጫው ተአማኒ ፣ ግልጽ እና ፍትሃዊ እንዲሆን ፣ ውጤቱም የመራጮችን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ እንዲሆን ይህ ሥርዓት አስፈላጊ ነው፡፡ ኢትዮጵያ ከቅርብ አመታት ወዲህ የምርጫ ስርዓቷን ለማሻሻል ከፍተኛ እርምጃዎችን የወሰደች ሲሆን ከእነዚህ ውስጥ በ2011 ዓም ተግባራዊ ያደረገችው አዲስ የምርጫ ህግ ማፅደቅ እና አዲስ ገለልተኛ የምርጫ ኮሚሽን ለማቋቋም ሙከራ ማድረግ በዋናነት ከሚጠቀሱት ውስጥ ናቸው፡፡ እነዚህ ማሻሻያዎች የምርጫውን ሂደት ግልፅነት ፣ ፍትሃዊነት እና አካታችነትን ለማሻሻልና የምርጫ ክርክሮችን ለመፍታት ኃላፊነት

ያለባቸው ተቋማትን አቅም ለማጠናከር ያለመ ተግባር ነው ለማለት ይቻላል፡፡

ሆኖም ግን በኢትዮጵያ ያለው የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት ሂደት ፍትሃዊ ፣ ግልጽ እና ውጤታማ እንዲሆን በምርጫ ህግ ማዕቀፍ ላይ መሰረታዊ ማሻሻያ ማድረግ ለነገ የማይባል ስራ ነው፡፡ በአሁኑ ሰዓት በኢትዮጵያ የምርጫ ህግ ማዕቀፍ ውስጥ እንደ ተግዳሮት ከሚወሰዱት መካከል ልዩ የምርጫ ስነ-ሥርዓት ህግ አለመኖር ፣ በምርጫ አዋጁ ላይ በፍርድ ቤት የሚሰጡ ውሳኔዎች የመጨረሻ መሆን አለመሆንን በተመለከተ የተገለፀ ነገር አለመኖር ፣ የምርጫ አዋጁ ከመራጮች ምዝገባና ከድምጽ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ የሚነሱ ቅሬታዎችን ስልጣን ያላቸው የፌደራል ወይም የክልል ፍርድ ቤቶች ያስተናግዳሉ በማለት የሚያስቀምጥ ቢሆንም ፍርድ ቤቶቹ የትኞች የክልል እና የትኞቹ የፌደራል ፍርድ ቤት እንደሆኑ የሚገልፀው ነገር የለም፡፡ ከዚህ በተጨማሪ የምርጫ አዋጁ አንቀፅ 149 እና 150 ስንመለከት የሥነ-ምግባር ጥሰቶችን በተመለከተ የፌደራል ከፍተኛ ፍርድ ቤት በቅድሚያ በመጀመሪያ ደረጃ ስልጣኑ የማየት እንዲሁም በመቀጠል ያንኑ ጉዳይ በይግባኝ ስልጣኑ መመልከት እንደሚችል ያመለክታል፡፡ እንዲሁም በኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ ከመራጮች ምዝገባ ፣ ከእጩ ምዝገባ ፣ ከድምፅ አሰጣጥ እና በድምጽ ቆጠራና ውጤት ጋር በተያያዘ በአዋጁ ከአንቀፅ 152-155 ስር የተመለከቱት የይርጋ ድንጋጌዎች ካለፉ አቤቱታ የማቅረብ መብቱ በይርጋ እንደሚታገድ ይገልፃለል፡፡ ይህም ከአቅም በላይ የሆኑ ምክንያቶች ቢኖሩም

ባይኖሩም የሚፈፀሙ ናቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በኢትዮጵያ ምርጫ አዋጅ ላይ የዕጩዎች ምዝገባን ተከትሎ በድሬዳዋና አዲስ አበባ ለሚነሱ ክርክሮች የትኛው የፍርድ ቤት በይግባኝ መመልከት እንደሚችል ግልጽ ድንጋጌ አያስቀምጥም፡፡ ይህም በምርጫ ሂደቱ ግራ መጋባትን ሊያስከትል እና እጩዎች ያለ አግባብ ከምርጫ ሂደቱ እንዲገለሉ ሊያደርግ ይችላል፡፡

በሚገባ የተነደፈ የምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት ሁሉም ብቁ መራጮች በምርጫው እንዲሳተፉ ፣ ምርጫው ፍትሃዊ እና ግልጽነት ባለው መልኩ እንዲካሄድ ፣ ውጤቱም የመራጮችን ፍላጎት የሚያንፀባርቅ እንዲሆን ይረዳል፡፡ሥርዓቱ አለመግባባቶችን ለመፍታት የሚያስችል መንገድ በማመቻቸት በምርጫ ሂደትና በዴሞክራሲያዊ ሥርዓቱ ላይ እምነትን ለመፍጠር ይረዳል፡፡ ስለሆነም በጠቅላላው እነዚህ በህግ ማዕቀፍ ውስጥ ያሉ ተግዳሮቶች ነቅሶ በማውጣት ለማሻሻል መሞከረ በምርጫ ክርክር አፈታት ሥርዓት ላይ ዘርፈ ብዙ ተፅኖችን የሚፈጥር ሲሆን እነሱም፤ **አንደኛው** የተሻሻለ የተጠያቂነት ስርዓትን ይፈጥራል፡፡ **ሁለተኛው** ደግሞ ግልጽነት የሚጨምር ሲሆን ይህም ክርክሮችን ለመፍታት ግልጽ የሆነ የጊዜ ሰሌዳ መስጠት ፣ ሁሉም አካላት ስለ ሂደቱ እና ስለተደረጉ ውሳኔዎች መረጃ እንዲያገኙ ማረጋገጥ እና የክርክር አፈታት ሂደቱን የበለጠ አሳታፊ ማድረግን ይጨምራል፡፡ **በሶስተኛ** ደረጃ የተሻለ ህጋዊነትን ይፈጥራል፡፡ በግልፅ አስቀድሞ የተደነገገ የህግ ማዕቀፍፍትሃዊ እና ግልጽነት ያለው የምርጫ ክርክር አፈታት ሂደት የምርጫ ሂደቱን ህጋዊነት ለማሳደግ ይረዳል፡፡ በምርጫው ውስጥ የሚሳተፉ ሁሉም ወገኖች በክርክር አፈታት ሂደት ላይ እምነት ካላቸው የምርጫውን ውጤት

ለመቀበል የበለጠ እድል አላቸው፡፡ ከዚህ በተጨማሪ በዋናነት የተሻለ እምነት እንዲፈጠር ይረዳል፡፡ ይህም በፖለቲካ ፓርቲዎች ፣ በህዝብ እና በምርጫ አስተዳደር ኃላፊነት ባለው የምርጫ አስፈፃሚ አካል መካከል መተማመን መፍጠርን ይጨምራል፡፡ እንዲሁም ዴሞክራሲን ያጠናክራል፡፡

## 4.2. የመፍትሄ ሃሳቦች

የምርጫ ክርክር አፈታት ስርዓት የማንኛውም የዴሞክራሲያዊ ሂደት ወሳኝ ገጽታ ነው፡፡በኢትዮጵያ የምርጫ ክርክሮች አፈታት ሂደት ላይ ለውጥ ለማምጣት በርካታ ተግባራ ሊከናወኑ ይገባል፡፡ ከእነዚህም ውስጥ

- ልዩ የምርጫ ክርክር መፍቻ ሥነ-ሥርዓት ሕግ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡አጠቃላይ የምርጫ ክርክር የሚመራበት ልዩ የሥነ-ሥርዓት ሕግ ተግባራዊ ማድረግ ክርክሮችን ለመፍታት ሂደቶችን ፣ አካሄዶችን እና ዘዴዎችን በግልፅ ያስቀምጣል፡፡ይህም ወጥነት ያለው ፣ ግልጽነት የተላበሰ እና ፍትሃዊነትን ለማረጋገጥ የሚያስችል ስርዓት ለመገንባት ይረዳል፡፡
- የምርጫ ክርክሮች ወደ ፍርድ ቤት የሚመጡበት አግባብ ግልጽ በሆነ መንገድ ሊቀመጥጡ ይገባል፡፡ የምርጫ ክርክሮች ወደ ፍርድ ቤት መጥተው ሲታዩ የሚመጡበት አግባብ በይግባኝ ነው ወይስ አይደለም እንዲሁም የምርጫ ክርክሮች ስልጣን በተሰጠው ፍርድ ቤት ታይተው ውሳኔ ካገኙ በኋላ ለሰበር መቅረብ ይችላሉ ወይስ አይችሉም እንዲሁም ከመራጮች ምዝገባና ከድምጽ አሰጣጥ ጋር በተያያዘ የምርጫ ክልል ቅሬታ ሰሚ ኮሚቴዎች በሚሰጡት ውሳኔ ላይ

የሚነሱ ቅሬታዎችን ስልጣን ያላቸው የትኞች የክልል እና የትኞቹ የፌደራል ፍርድ ቤት እንደሆኑ እንዲሁም የዕጩዎች ምዝገባን ተከትሎ በድሬዳዋና አዲስ አበባ ለሚነሱ ክርክሮች የትኛው የፍርድ ቤት በይግባኝ መመልከት እንደሚችል ግልጽ በሆነ መንገድ የአዋጁን ድንጋጌዎቹን በማሻሻል ሊቀመጡ ይገባል።

- ግልጽ የሆነ የዳኝነት ስልጣን ድልድል ሊኖር ይገባል፤

የምርጫ ክርክሮችን ለመፍታት ኃላፊነት በተሰጣቸው የተለያዩ ፍርድ ቤቶች መካከል ያለው የዳኝነት ስልጣን አቀማመጥ ግልጽ መደረግ መቻል አለበት። ይህም የምርጫ ክርክር አፈታት ሂደቱን ለማሳለጥ እና ውዥንብርን ለመከላከል ያስችላል።